# እድገቱ ለማን ነው? አዲስ ትርጉም የሚያስፈልገው የልማት መርህ

ከአክሎግ ቢራራ (ዶር)

**“If all economists laid end to end, they will not reach a conclusion.”**

**George Bernand Shaw**

## ክፍል አንድ

ትኩረቱ

ባለፉት አስር ዓመታት፤ ማለትም፤ ከምርጫ ዘጠና ሰባት በኋላ፤ ኢትዮጵያ ፈጣን እድገት እንዳሳየች እቀበላለሁ። የፈጣን እድገቱ ትኩረት መንግሥት ባካሄደው በመሰረተ ልማት--መንገዶች፤ ድልድዮች፤ ትምህርት ቤቶች፤ የጤና ጣቢያዎች፤ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፤ የመብራት ኃይል ማመንጫ ግድቦች፤ የሃዲድ መንገዶች፤ ፎቆች፤ ቪላዎችና ከዚህ ጋር የተያያዙ ከተሞች ወዘተ ከመስፋፋት ላይ ነው። ሃገሪቱ ዘመናዊ እድገቷን ከዝቅተኛ ደረጃ ላይ ስለጀመረች እድገቱ ግዙፍ እንደሚመስል አይካድም። “አስደናቂው” እድገት በተከታታይ የተካሄደው ከምርጫ ዘጠና ሰባት ወዲህ ነው። አንደኛው የማስተናግደው ጥያቄ ኢትዮጵያ ይኼን እድገት ምን ግብዓት አግኝታ ስኬታማ ለማድረግ ቻለች? የሚለው ነው። ሁለተኛውና ቁልፉ ጥያቄ የእድገቱ ውጤት ዋና ተጠቃሚ ማነው? የሚል ነው። መልካም አስተዳደር ነጻነትን፤ ሰብእነትን፤ ፍትህን፤ የህግ የበላይነትን፤ ግልፅነትን፤ ተጠያቂነትን፤ ሃላፊነትን፤ ተሳታፊነትን ወዘተ የሚያካትት የመንግሥት ስርዓትና የአስተዳደር ጥያቄ ነው። ሁሉም ኢትዮጵያዊያን የእድገቱ ውጤት ተጠቃሚ ሊሆኑ የሚችሉት መልካም አስተዳደር ሲኖር ነው ተብሎ የሚተቸው በዚህ ምክንያት ነው።

ከቀድሞዎቹ የኢትዮጵያ መንግሥታት ጋር ሲነጻጸር ለትግራይ ሕዝብ ነጻ አውጭ ግንባር (ህወሓት) ብቸኛ የፖለቲካ የበላይነት ለሚያሽከረክረው የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዬታዊ ዲሞክራሳዊ ግንባር (ኢህአዴግ) መንግሥት በኢትዮጵያ ረዢም ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ እርዳታ የምእራብ መንግሥስታትና የሚቆጣጠሯቸው ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ለግሰዋል። ስደተኛውም ወገኑን ለመርዳትና የራሱን ኑሮ ለማሻሻል የለገሰውና ያፈሰሰው መዋእለንዋይ የሚናቅ አይደለም። ስለሆነም፤ በኢትዮጵያ እድገትና እየጨመረ በሄደው የውጭ ለልማት ይውላል ተብሎ በተሰጠው እርዳታ መካከል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት እናያለን። በ1997/1998 $675 ሚሊየን የነበረው ለልማት የተሰጠ እርዳታ በ2006 ወደ $1.9 ቢሊየን፤ በ 2012 ወደ $4 ቢሊየን፤ ከዚያ ወዲህ ያለው በዓመት በዝቅተኛ $4 ቢሊየን ደርሷል። ስለዚህ በመሰረተ ልማት የሚታይ፤ የሚዳሰስ እድገት ባይኖር አከራካሪ ይሆን ነበር እላለሁ። ገዢው ፓርቲ የሚታይ መሰረተ ልማት ስኬታማ ባያደርግ እርዳታው እየጨመረ አይሄድም ነበር። በአብዛኛው ለልማት አስፈላጊ የሆነው መሰረተ ልማት እየተስፋፋ ሲሄድ አብሮ የሚራመደው መዋቅራዊ ለውጥና የሕብረተሰቡ ኑሮ መሰረት ይይዛል። በዋናው መስፈርት ሳየው፤ የአብዛኛው ሕዝብ ኑሮ እየተሻሻለ ይሄዳል፤ ሕዝቡ በመንግሥት መሪዎች ላይ እምነት ይኖረዋል፤ ከተፈጥሮ የሚመጣን እርሃብ ለመቋቋም ይቻላል፤ ገቢ እያደገ ስለሚሄድ መንግሥት ከታክስና ከሌላ የሚያገኘው ገቢ እያደገ ይሄዳል፤ በውጭ አበዳሪዎች፤ መንግሥታትና ለጋሶች የሚኖረው ጥገኝነት እየቀነሰ ይሄዳል። ከአገር እየሸሸ የሚሄደው የወጣቱ ትውልድ ቁጥር እየቀነሰ ይሄዳል ወዘተ። ከተፈጥሮ የሚከሰት ረሃብተኛ ቁጥር እየቀነሰ ይሄዳል። ዲሞክራሳዊ አገዛዝ ጠንካራ ሆኖ የአገሪቱ የምርት ውጤት እየጨመረ ሲሄድ ከድርቅ የሚከሰትን ረሃብ ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠር ይቻላል። ይኼ የማይካድ ሁኔታ ከቀጠለ ኢትዮጵያ የቱኒሺያና ሌሎች የአረብ አገሮች የደረሰባቸው ሁኔታ ይደርስባታል። ኪራይ ሰብሳቢነት፤ የቡድንና ሌላ አድልዎ፤ ሙስና፤ የአስተዳደር በደል፤ የሰብአዊ መብቶች መገፈፍ ወዘተ መንግሥታትን እንደሚያንበረክክ የሚያከራክር አይመስለኝም።

የመሰረተ ልማት መስፋፋት እንዳለ ሆኖ፤ በዚህ ትችት የማቀርበው ክርክርና ትንተና ባለፉት ሃያ አራት ዓመታት በህወሓት ብቸኛ የበላይነት የሚመራው የኢህአዴግ እድገታዊ መንግሥት አስገኘሁት የሚለው ‘አስደናቂ’ የእድገት ውጤት ለጥቂት ደላላዎች፤ ነጋዴዎችና የወፍ ዘራሽ ኃብታሞች ከፍተኛ ገቢና ኃብት አስገኝቷል፤ ጎሳዊ አድልዎን፤ የአስተዳደር ብልሽትን፤ የተዛባ ገቢንና እድገትን፤ ኪራይ ሰብሳቢነትን፤ ድርጅታዊ ምዝበራን፤ ሙስናንና ከሕግ ውጭ ከሃገር የሚሸሸውን ኃብት መጠን ወደ አደገኛ ደረጃ አሸጋግሮታል የሚል ነው።

በተጨማሪ፤ የኢትዮጵያ የመንግሥት ወይንም የአገዛዝ ስርዓት (Government and State) ጠባብና ጎሰኛ በሆኑ ክፍሎች መማረኩ ለአብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ተመጣጣኝ ተሳትፎና የእድገት ውጤት ተጠቃሚነት ማነቆ ሆኗል። የምከራከረው ኢትዮጵያ እንደ አገር ያላትን የተፈጥሮና የማህበረሰብ ጥሪቶች፤ የውጭ እርዳታ፤ ከስደተኛው የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬና ሌላ ግብዓት ሙሉ በቡሉ ተጠቅማ የስራ፤ የገቢ እድገትና የኃብት ክምችት እድል ለሁሉም ዜጎቿ ለማቅረብና የምርት ውጤቶቿን ለመጨመረ የምትችለው ሁሉም ዜጎች የሚሳተፉበትና ጥቅም የሚያገኙበት የእድገት መርህ መሰረት ሲይዝና የሕግ ዋስትና ሲኖረው ነው። ሕዝብን የእድገቱ መዓከል ያደረገ አገዛዝ ከሕዝቡ የሚፈራው ነገር የለም፤ ያላደረገ አገዛዝ ዙሮ ዙሮ፤ ጊዜ ቢወስድም በሕዝብ ቁጣና እምቢተኛነት ይንበረከካል። ኢትዮጵያ ታላቅ አገር እንድትሆን፤ መላው ሕዝቧ ከአሰቃቂ ድህነትና ኋላ ቀርነት ዑደት (vicious cycle) ነጻ ወጥቶ ጤናማ ኑሮ እንዲኖር ጥረት ማድረግ የሁላችንም ሃላፊነት ነው። በእኔ ግምት በጎ ፈቃደኝነት ካለ ይኼ ይቻላል። ይኼን ታሪካዊ ሃላፊነት ለመወጣት የምንችለው ተቃዋሚው፤ መላው የማህበረሰብ ክፍልና ገዢው ፓርቲ አብረው የሚሰሩበት የፖለቲካ ሁኔታ ተመቻችቶ ሁሉን አቀፍ፤ ፍትሃዊ፤ አሳታፊ፤ ሰላማዊና ዲሞክራሳዊ የሆነ አገዛዝ እንዲመሰረት የጋራ ጥረት ማድረግ ነው። በርማ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናት። ጋና ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናት ወዘተ።

ተግዳሮቶቹ የስርዓት ናቸው፤ የግለሰብ አይደሉም

ሰሞኑን በአገር ቤትና በውጭ ኢትዮጵያዊያንን የሚያነጋግረው አስኳል ጉዳይ በጠቅላይ ሚንስትር ኃይለማሪያም ደሳለኝ የሚመራው ኢህአዴግ በራሱ ፈቃድ ሞያተኞችን ተጠቅሞ ስለ መልካም አስተዳደር ያደረገው ሰፊና ጥልቀት ያለው ጥናት፤ ግኝትና ውይይት ነው። ይኼ ከዚህ በፊት ያልታሰበና ያልታየ ብሄራዊ ጥናትና ምርምር አሁን ለምን ተደረገ? የሚለው ጥያቄ አግባብ ቢኖረውም እኔ ለጥያቄው መልስ ለመስጠት አልፈልግም፤ አልሞክርም። ቁም ነገሩ ባለሞያዎቹ መሰረታዊ ተግዳሮቶችን መርጠው በሶስት ወራት የሰበሰቡት መረጃ፤ ያነጋገሩት የሕህብረተሰብ ስርጭት አግባብነት፤ ያቀረቧቸው ግኝቶች እጅግ በጣም አስደናቂና የሕዝብን ብሶት የሚያንጸባርቁ መሆናቸው ነው። በእኔ ግምት አንዳንድ ባለሥልጣናት እንዳሉት፤ ያቀረቡት የችግሩን ጫፍ እንጅ ሁሉንም አይደለም። ፈረንጆች እንደሚሉት “This is the tip of the iceberg.” በምንም አይነት መስፈርት ባየው ይኼን የመሰለ ያልታሰበ ምርምርና ጥናት ለሕዝብ ይፋ ማድረግ የሚመሰገን እንጅ ለድለላና ለሺንገላ ነው የሚል ግምት የለኝም። እርግጥ ነው፤ የውጭ ተቋሞች---ዓለም ባንክ፤ የተባበሩት መንግሥታት የልማት ድርጅት፤ ግሎባል ፋይናንሺያል ኢንተግሪቲ፤ ዩንቨርስቲ ኦፍ ማሳቹሴትስና ሌሎች በኪራይ ሰብሳቢነት፤ ጉቦ፤ አድልዎ፤ ሙስናና ከአገር በገፍ የሚሸሽ ግዙፍ ኃብት ጥናቶች አድርገው ለውጥ አልታየም። ሁኔታው እየተባባሰ ሂዶ የሕዝብ ምሬት ወደ አደገኛ ደረጃ ተለውጧል። ስለዚህ፤ ተመልካቾች ጥናቱ “የሺንገላና የሕዝብ ማባበያ ነው” ቢሉ አይፈረድባቸውም። ሆኖም፤ ሁሉን ነገር እየተጠራጠርንና እየተቸን እድሎችና የለውጥ ክፍተቶች እንዲያመልጡን ማድረግ በታሪክ ያስጠይቀናል። ከዚህ በፊት ተከታታይ የዲሞክራሳዊ አገዛዝ ስርዓት ለውጥ እድሎች ያመለጡን በምን ምክንያት ነው? የሚለውን ጥያቄ ማስተናገድ አለብን እላለሁ። በአጭሩ ሃሳባችን ለመለወጥ ፈቃደኛ ስላልሆንና ተባብረን ለመስራት ስላልቆረጥን ነው።

ምስጋና

በመጀመሪያ ጥናቱን ላካሄዱት ባለሞያዎች አድናቆቴንና አክብሮቴን አገልጻለሁ። ጠቅላይ ሚንስትሩ የጀመሩት ውይይት እየሰፋ ሂዶ፤ <u>ሰፊውን ሕዝብና የተቃዋሚውን ክፍል አሳትፎ</u> ወደ ዋናው መሰረታዊ ወይንም ስርዓት ወለድ የአገዛዝ ሁኔታ እንደሚሸጋገር ያለኝን ተስፋና ምኞት እገልጻለሁ። ይኼን የምልበት ምክንያት፤ የችግሩ መጠን፤ ጥልቀትና ስፋት በጥገና ሊለወጥ የማይችል መሆኑን ስለተረዳሁና የሁሉም ኢትዮጵያዊያን ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን ስለማምን ነው። ይኼን በሚመለከት ጠቅላይ ሚንስትሩ የተናገሩት የችግሩን ጥልቀት ያሳያል። <u>“ችግሩን የፈጠርነው እኛው ነን፤</u> እራሳችን ልዩ ልዩ የጥቅም ሰንሰለቶች (network of beneficiaries) ስላሉን፤ እነሱ እንዳይፈርሱብን ወይንም እንዳይነኩ አሁን በስብሰባ ላይ የተነጋገርነውንና የተስማማንበትን ጉዳይ ከስብሰባው ስንወጣ በተግባር እንዳይገለጽ እናደርጋለን።” በስብሰባው ከተገኙት የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት መካከል በኪራይ ሰብሳቢነት፤ በጉቦ፤ በጎሳዊ አድልዎ፤ በሙስና በሥልጣን ብልግና የተበከሉ ግለሰቦች እንደነበሩ ይነገራል። እነዚህ ግለሰቦች ድርጅቶቻቸውን ሽፋን አድርገው ማንኛውም ሕዝብን የሚጠቅም ለውጥ እንዳይመጣ እንደሚያርጉ እገምታለሁ። ይኼ ከሆነ ከገዢው ፓርቲና ከመንግሥት ተወካዮች ውጭ አግባብ ያላቸውን ተቋሞችና ግለሰቦች ያላሳተፈው ጥናት አበዳሪዎችን፤ የውጭ መንግሥታትንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመሸንገል የተደረገ ጥናት ነው የሚለውን ትችት ያጠናክረዋል። ያም ሆነ ይህ፤ ጥናቱ እንዳሳየው በጸረ ሙስናና ሌላ የሕግ አስፈጻሚነት ስራ የተሰማሩት ሰራተኞች የሚከላከሉትና ለፍርድ የሚያቀርቡት ዝቅተኛውን “ወንጀለኛ ወይንም ኪራይ ሰብሳቢ” ነው። ዋናዎቹ ከፍተኛ ኪራይ ሰብሳቢዎች በራሳቸው ላይ ትችት አቅርበው በራሳቸው ላይ ክስ ለማቅረብ የሚችሉ አይመስለኝም። መንግሥትና ገዢው ፓርቲ ከቁንጮው የተሰገሰጉትን ከፍተኛ ባለሥልጣናትና ኪራይ ሰብሳቢዎች አይነካቸውም። አንድ

ታዛቢ እንዳስቀመጠው "መንግሥትና ገዢው ፓርቲ የከፍተኛ ኪራይ ሰብሳቢዎችና ጉበኞች መከታ፤ ምሺፍና ሺፋን ሆኗል። " ውይይቱ መልካም ነው፤ ከውይይቱ በኋላስ እያንዳንዱ ባለሥልጣን ወደ ፈጠረው "የጥቅም ሰንሰለት" ይዞራል ወይንስ አይዞርም? የሚለው ጥያቄ በድርጊት ይታያል።

አስኳል የአስተዳደር ችግሮችን ስገመግም ደላላዎች በቀን ብዙ ሚሊየን ብር ካፒታል ያሽከረክራሉ፤ የአየር በአየር ንግድ ተስፋፍቷል፤ ከቀረጥ ነጻ የሆነ ንግድ ይካሄዳል፤ የጥቁር ገበያና በአጭር ጊዜ ሳይሰሩ መክበር ተቋማዊ ሆኗል። መንግሥት የሚገባውን ቀረጥና ሌላ የአገር ውስጥ ገቢ ለመሰብሰብ አልቻለም። የፍርድ ስርዓት የሚተዳደረው በጉቦ ነው። አገልግሎት የሚሰጠው በጉቦና በወገን መረብ ነው " ወዘተ ሲባል መንግሥት የለም ወይንስ አለ ወደሚል ጥያቄ ያመራኛል። እንደ ኢትዮጵያ ባለ አንድ ፓርቲ በሚቆጣጠረው አገር ደላላዎች በተናጠል ወንጀል ለመስራት አይችሉም። አንድ ተራ ሰው በማግስቱ ሚሊየኔር አይሆንም። ከደላላዎቹ ጀርባ ባለሥልጣናት መኖራቸው ግልጽ ነው። የጥቅሙ ዘግናኝነት፤ የሞራል ውድቀቱና የብልግናው መረብ ከአገዛዙና ከባለሥልጣናት ጋር የተያያዘ ነው። ይኼን አደጋ በመመልከትና መፍትሄ እንዲፈለግበት በማሰብ "ድርጅታዊ ምዝበራ" የተባለውን መፅሃፌን በኢትዮጵያ እንዲታተም ሞክሬ አልተሳካም። አሁን ላለው ውይይት ይረዳል የሚል እምነት ስላለኝ፤ ታትሞ እንዲሰራጭ ቢደረግ ይጠቅማል።

የችግሩን ጥልቀትና ስፋት በአንክሮ ለሚመለከት ኢትዮጵያዊ ጥገናዊ ሳይሆን መሰረታዊ ለውጥ አስፈላጊ ነው እላለሁ። የባለሞያዎቹ ጥናት እደሚያሳየው "የስብሰባዎች ወረርሽኝ" የአገዛዙ መለያ ሆኗል። ለዚህ ብቻ የሚፈሰው ባጀት ትንንሽ ፋብሪካዎች ይሰራ ነበር። "ወረርሺኙ" ግልፅነት፤ ተጠሪነትና ሃላፊነት እንዲደበቅ፤ ማን ምን እንደሰራ እንዳይታወቅ፤ ዜጎች በቀጠሮ እንዲጉላሉ፤ ውሳኔ እንዳይደረግ ወዘተ ሲያደርግ ቆይቷል። ቅልጥፍናን አድክሟል። ሕብረተሰቡ በመንግሥት ላይ ያለውን እምነት በርዞታል። ስለዚህ ነው፤ የደርግ አይነት "ዘመቻ" እና ግምገማ ስኬታማ ለውጥ ሊያመጣ እይችልም የምለው። "ዘመቻ" ቢደረግ በማን ላይ ነው የሚዘመተው? በምን አበይት ጉዳዮች ላይ? ማንን ይለያል? ችግሩ ከከፍተኛ የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት ጋር የተያያዘ ከሆነ፤ ማን በማን ላይ ይዘምታል? ከተዘመተስ በኋላ ውጤቱ ምን ይሆናል? ማን ከሕግ በላይ ሆኖ እንዳይነካ ይደረጋል? በኢህአዴግ ውስጥ ያሉ አባል ፓርቲዎች በአንድ ድምጽ ሰርተው ማንኛውንም ወንጀለኛ ለፍርድ ለማቅረብ ተዘጋጅተዋል ወይንስ አልተዘጋጁም? የዚህ አደጋስ ምንድን ነው? ወዘተ የሚሉትን ጥያቄዎች አነሳለሁ። ጥያቄዎቹ መሰረታዊ ለውጥን የሚመለከቱ ናቸው።

መሰረታዊ ለውጥ ስል ማንኛውም የመንግሥት ባለሥልጣን ከሕግ በላይ መሆን የለበትም ማለቴ ነው። እውነተኛ ዲሞክራሳዊ አገዛዝ ለመመስረት በሩ ክፍት መሆን አለበት ማለቴ ነው። የሕዝብ ተቋሞች፤ ለምሳሌ የማህበረሰብ ድርጅቶች ነጻ ይሁኑ ማለቴ ነው፤ የመገናኛ ብዙሃ ነጻ ይሁኑ ማለቴ ነው። ያለምንም ማስረጃ የታሰሩ ኢትዮጵያዊያን ይለቀቁ ማለቴ ነው። ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ጉቦ፤ አድልዎ፤ ሙስናና ከሃገር እየተሰረቀ የሚሸሸው ግዙፍ ሃብት ይቁም፤ ቢቻል ይመለስ፤ ወንጀል የፈጸሙት በሕግ ይጠየቁ፤ ሕግ በጉቦ፤ በአድልዎና በወገን ትሥስር አይሰራ ማለቴ ነው። ሁሉም የፓርቲ፤ የመንግሥትና ሌሎች ባለሥልጣናት ያላቸውን የግልና የቤተሰብ ገቢና ኃምብት መጠንና የኃብቱን የሴክተር ስርጭትና ቦታ ለሕዝብ ይፋ ያድርጉ ማለቴ ነው። በአጭሩ የኢትዮጵያ የአገዛዝ ስርዓት በቅርቡ ነጻና ፍትሃዊ ምርጫ እንዳካሄደችው እንደ በርማ እንዲሆን አመቻች ሁኔታ ይፈጠር ማለቴ ነው ወዘተ። ፕሬዝደንት ኦባማ ኢትዮጵያን ሲጎበኙ ያነሷቸው እነዚህን የመሳሰሉትን የዲሞክራሲ ጥያቄዎችን ነበር። የዚህ አይነት ሂደት የአመራር ደፋርነትንና ቆራጥነትን ይጠይቃል። ባለሞያዎቹ ያሳዩትን ቆራጥነትና ድፍረት የመንግሥትና የፓርቲ ባለሥልጣናት ቢያሳዩ እመርታዊ ለውጥ የሚመጣበት ድልድይ ይሰራል የሚል እምነት አለኝ።

የኢትዮጵያ የእድገት መርህ ዛሬ ማነቆ ሆኖ ስራ የመፍጠርና የማምረት ኃይሏን ያገበው የመንግሥት ወይንም የአገዛዝ አድካሚነትና ብልሹነት ነው። ለምሳሌ፤ እጥፍ እድገት አለ በሚባልባት አገር አስራ አምስት ሚሊየን ሕዝብ እየተራበ ነው። የምግብ ራስን መቻል ጥረት ስኬታማ ያልሆነበት የፖሊሲ፤ የመዋቅር፤ የቴክኖሎጅ፤ የባህል ወዘተ ምክንያት ለውይይት መቅረብ አለበት። ሕዝቡ ድምጽ ስለሌለው፤ ተቃዋሚ ፓርቲዎች ስለተበታተኑ፤ ስለተከፋፈሉ፤ ስለታፈኑ ወዘተ፤ ከመንግሥት ቁጥጥር ነጻ የሆኑ የመገናኛ ተቋሞች ስለሌሉና ነጻ ጋዜጠኞች ስለታሰሩ ወይንም ከሃገር ሸሽተው ስለወጡ፤ የማህበረሰብ ድርጅቶች ፈጽሞ ስለፈራረሱ፤ ነጻ የሞያ ድርጅቶች ስለሌሉ የእድገቱ እውነተኛ ገጽታና ውጤት ሊታወቅ አልቻለም። ይኼን የምልበትን ምክንያት ለማጠናከር እፈልጋለሁ። ዓለም ባንክ **The Road to 2050: Sustainable Development for the 21st Century** በተባለው የታወቁ ባለሞያዎች ባቀረቡት አቅጣጫ አመልካች ጽሁፍ እንዲህ ይላል። "**Governance is a major constraint on development today, and rectifying this will require both institutional reforms, and the mobilization of civil society.**" ከላይ የጠቀስኩት በባለሞያዎቹ የቀረበው ትንተናና ትችት ይኼን አመልካች ጽንሰ ሃሳብ ያንፀባርቃል፤ በኢትዮጵያዊያን መቅረቡ ያስመሰግናል። መልካም አስተዳደር ዘላቂነት ላለውና ፍትሃዊ ለሆነ እድገት ወሳኝ ነው። ከሆነ፤ የፓርቲና የመንግሥት ባለሥልጣናት በሕዝብ ድምጽና በሕዝብ የስልጣን የበላይነት ማመን አለባቸው። "የማህበረሰቡን ክፍል ማንቀሳቀስ" ለዘላቂና ለፍትሃዊ እድገት ወሳኝ ነው ሲባል የሚገባኝ ነጻነት ይኑር፤ ሰብአዊ መብቶች ይከበሩ፤ የሕግ የበላይነት ይኑር ወዘት ማለት ነው። ልማት በአዋጅና በዘመቻ፤

ልማት በማስፈራራት፤ ልማት በኃይል መሰረት ሊይዝ አይችልም። የሕዝብ ፈቃደኛነት፤ ተሳትፎ፤ ባለቤትነትና የሚታይ ጥቅም መኖር አለበት። የእርሻን ምርት ለመጨመርና አካባቢን ለመንከባከብ ገበሬው የራሴ ነው የሚለው ኃብት መኖር አለበት። ዓለም ባንክ ካቀረበው የመልካም አገዛዝ አስፈላጊነት ፅንሰ ሃሳብ አከራካሪው ነጥብ እንደሚከተለው ነው።

ለኢትዮጵያ ፈጣን እድገት ከፍተኛ ግብአት ያደረገው የውጭ እርዳታ ነው። እንደ ዓለም ባንክ ያሉ ለጋስ ድርጅቶችና መንግሥታት ለምን የሚያምኑበትን የአገዛዝ ማነቆነት እንዲፈቱ፤ ራሳቸው ማነቆ እንዳይሆኑ ጫና አያደርጉም? የሚል ጥያቄ አግባብ አለው። **“Development assistance, partnered with good governance in recipient countries, can be a powerful engine for growth….human capital energy, infrastructure, agricultural productivity, aid and trade, will clearly be essential for achieving a wealthier, more equitable by 2050.”** አሁን ባለው ሕዝብን መአከል ያላደረገ የኢትዮጵያ የአገዛዝና የእድገት ሁኔታ ኢትዮጵያ ይኼን ራእይ ስኬታማ ለማድረግ የምትችል አይመስለኝም። በኪራይ ሰብሳቢነት የተበከለ የፖለቲካ፤ የኢኮኖሚና የማህበረሰብ አገዛዝ ስር ነቀል የሆነ የበላይነት የሚያካሂደውና የእድገት ጥቅሞችን በአብዛኛው ለጥቂቶች የተሳሰሩ ቡድኖችና ታማኞች የሚያሽጋግረው ብሄራዊ የሆኑ ተቋሞችን ሙሉ በሙሉ በማጥፋት ነው። ለምሳሌ፤ ጠባብ ጎሰኛነትና ደላላነት አግባብ አለው የሚለው ሂደት ዋጋ ይከፈልበታል። ከገበያ ውድድር ጋር አብሮ አይሄድም። ውድድር በግልጽና ህጋዊ በሆነ ደንብ የሚካሄድ ጉዳይ ነው። ኪራይ ሰብሳቢነትና ከዚህ ጋር የተያያዘው ደላላነት በግልጽና በህግ ሊካሄድ አይችልም። ተቋሞች የአንድ ፓርቲ አገልጋይ እስከሆኑ ድረስ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍሎች ሊያገለግሉና ድምጻቸውን ሊሰሙ አይችሉም። ባለ ሥልጣናቱና ባለ ኃብቶቹ ተደጋግፈው አሸናፊውን ይመርጣሉ። ጠቅላይ ሚንስትሩ ያሳሰቡት ይኼ እንዳይሆን ነው። ከመንግሥት ቁጥጥር ነጻ የሆኑ የማህበረሰብና የሞያ ድርጅቶች፤ የመገናኛ ብዙሃን ፍጹም በሆነ ደረጃ ስለወደሙ ወይንም ስለታፈኑ፤ የሕዝብ ድምፅና መብት አብሮ ታፍኗል፤ አብሮ ወድሟል። ክትትል የሚያደርግ ነጻ ተቋም የለም። የዚህ አድካሚ ውጤት በመሬት ይታያል። ተራው ኢትዮጵያዊ በፖሊስና በባጀት አጠቃቀም ድምጽ እንዳይኖረው አግቦታል። በጎሳ ልሂቃን የበላይነት የተቀረፁ ተቋሞች የሚያገለግሉት የፈጠራቸውን የበላይ አካል ስለሆነ አንዱ ተቋም ሌላውን ሊገታው አይችልም። ስለዚህ፤ ሁሉን የሚያሳትፍ በጨዋነት የሚመራ ብሄራዊ ውይይት ያስፈልጋል። ይህ አገር አቀፍ ውይይት ተቃዋሚውንና የተገለለውን ክፍል ለማሳተፍ ካልቻለ መሰረታዊ ለውጥ አይቻልም። ጥገናዊ ለውጥ ይቻላል። አሁን ያለው የአገዛዝ ሁኔታ የሚያሳየው የሚያመዛዝን፤ ፍትህ የሚሰጥ (Checks and balances) የሚባል ነገር እንደሌለ ነው። የማህበረሰብ ድርጅቶች መፋፋት የፖለቲካ ወይንም የመንግሥት መልካም አገዛዝ ጥያቄ ነው። በእኔ አመለካከት፤ የኢትዮጵያን እድገት ከማህበራዊው፤ ከፖለቲካው፤ ከአስተዳደሩ፤ ከነጻነቱና ከሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ለይቶ ለማቅረብ አይቻልም። የአገዛዙ አፈጣጠር፤ አወቃቀርና አሰራር የተሳሰረ፤ የተቆላለፈና የተደጋገፈ ስለሆነ ችግሩም በስርዓቱ አድካሚነት መነጽር መታየት አለበት እላለሁ።

ባጠቃላይ የኢትዮጵያ መሰረታዊ ችግር የመንግሥት ወይንም የአገዛዝ መጥፎነት ነው። ስግብግብነት፤ በአጭር ጊዜ ማንኛውንም ነገር ሰርቶ መክበር፤ ለአገርና ለወገን አለመቆርቆር ወዘተ ባህልን የፈጠረው ስርዓቱ ነው። የአገዛዙ መርህና ተቋሞች ካልተለወጡ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው እድገት የሚቻል አይመስለኝም። ተቋሞች ይለወጡ ስል የሰብአዊ መብቶችና ነጻነት አይታገቡ፤ የስለላ መረብ ስር ነቀል በሆነ ደረጃ የአገዛዝ ስልት መሆኑ ይለወጥ፤ የህወሓትና ተቋሞቹ ሞኖፖሊዎች ይፋ ሆነውና ተወግደው ወይንም ተለውጠው የግል የኢኮኖሚ ውድድር እንዲስፋፋ ይደረግ፤ ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ድርጅታዊ ምዝበራ፤ ጎሳዊ አድልዎ፤ ጉቦ፤ ሙስና ከሃገር ተሰርቆ የሚሸሽ ግዙፍ ሃብት ህጋዊ ክትትል ይደረግበት ማለቴ ነው። ዓለም ሊክደው የማይችለው አበይት ጉዳይ፤ “እድገት አለ” ቢባልም የኢትዮጵያን ሕዝብ ስቃይ የሚያሳዩ መስፈርቶች እየባሱ እንጅ እየተሻሻሉ አለመሄዳቸውን ነው። የኢትዮጵያን ሁኔታ ከአሜሪካኖች የበለጠ የሚከታተልና የሚያውቅ የለም። የአሜሪካ “ በጎ አድራጊዎች” ኢትዮጵያን ወረዋታል የሚሉ ብዙ ታዛቢዎች አሉ። እነዚህ “በጎ አድራጊዎችና ባለሞያዎች” መልካም አስተዳደርን ፈጽሞ አይነኩትም። የሚያስተናግዱት የራሳቸውንና የሚወክሉትን አገር ጥቅም ነው። የአሜሪካ መንግሥትም ዘገባዎች ከማውጣት ሌላ ጥርስ ያለው ውሳኔ አያደርግም። በ**June 25, 2015 U.S. Department of State, 2014 Reports on Human Rights Practices** በሚል አርእስት ያቀረበው ዘገባ የኢትዮጵያን ሕዝብ አሰቃቂ ሁለገብ ሁኔታ ያሳያል። **“The most significant human rights problems included restrictions on freedom of expression, including continued restrictions on print media and on the internet, and restrictions on freedom of association, including through arrests; politically motivated trials; and harassment and intimidation of opposition members and journalists. The government continued restrictions on activities of civil society and nongovernmental organizations (NGOs) imposed by the Charities and Societies Proclamation (the CSO law).”** በእኔ እምነት ህወሓት/ኢህአዴግ ተቃዋሚዎቹን ሁሉ የሚቀጣበት **Anti-Terrorism Proclamation**ምም አብሮ መታየት አለበት። ሁለቱ ህጎች በሰላም ሆነ በሌላ የሚቃወመውን ግለሰብ ሁሉ መቅጫ መሳሪያ ሆነው ያገለግላሉ። በዚህ መሰረት ገዢው ፓርቲ ለስልጣኑ ተወዳዳሪ ወይንም አስጊ የሆነውን ግለሰብ ሁሉ በፈጠራ መረጃ ከሶ ያስቃያል። በሌላ በኩል ሃብት ያለውና ከገዢው ፓርቲ ባለሥልጣናት ጋር ቁርኝት ያለው ግለሰብ ወህኒ ቤት አይገባም፤ ቢገባም ይለቀቃል፤ ስራውን ሰርቶና ኃብቱን ይዞ፤ ልጆቹን አስተምሮ ይኖራል። ጠበቃዎች በሞያቸው ከመከራከር ይልቅ “ዛሬ ይኼን ጉዳይ ማን ይዳኛል” ብለው ሲጠይቁ ፍርድ በግንኙነትና በጉቦ እንጂ በሕግ አግባብነት የማይተዳደርና የማይስተናገድ መሆኑን ያሳያል።

ከታች የምጠቅሰው የአሜሪካ መንግሥት የደመደመው ግፍ ሊካሄድ የቻለው ገዢው ፓርቲ መላው የሰለጠነው ዓለም ከሚቀበለው ሕግና የራሱ ሕገ መንግሥት መመሪያው አድርጎ የደነገገውን መብቶች ሁሉ ዋጋ ቢስ በማድረግ መሆኑን ያሳያል። ባጭሩ፤ ዘገባው "የቻይና፤ የግብፅ፤ የኤርትራ፤ የኢትዮጵያ፤ የኢራን፤ የራሽያና የሳውዲ አረቢያ መንግሥታት የነጻነት፤ የነጻ መገናኛ ብዙሃን፤ የነጻ ማህበረሰብ ድርጅቶች ወዘተ ፀርነት" ቀጥለው "አፈናውን እንዳባባሱት" ያሳያል። ይኼን የሚያካሂዱት "ጋዜጠኞችን፤ ብሎገሮችን፤ በሰላም የሚታገሉ የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ሁሉ በማሰር፤ በመደብደብና በማሰቃየት" ነው ይላል። **"Other human rights problems included alleged arbitrary killings; alleged torture, beating, abuse, and mistreatment of detainees by security forces; reports of harsh and at times life-threatening prison conditions; arbitrary arrest and detention; detention without charge and lengthy pretrial detention; a weak, overburdened judiciary subject to political influence; infringement on citizens' privacy rights, including illegal searches; alleged abuses in the implementation of the government's "villagization" program; restrictions on academic freedom; restrictions on freedom of assembly, association, and movement; alleged interference in religious affairs; limits on citizens' ability to change their government; police, administrative, and judicial corruption; violence and societal discrimination against women and abuse of children; female genital mutilation/cutting (FGM/C); trafficking in persons; societal discrimination against persons with disabilities; clashes between ethnic minorities; discrimination against persons based on their sexual orientation and against persons with HIV/AIDS; limits on worker rights; forced labor; and child labor, including forced child labor. Impunity was a problem. The government, with some reported exceptions, generally did not take steps to prosecute or otherwise punish officials who committed abuses other than corruption."** ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ጉቦንና ሙስናን በሚመለከትም ቢሆን ከኢትዮጵያ ገዢ ፓርቲ፤ በተለይ ከህወሓት ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት ከሌላቸው በዝቅተኛ ሙስና የተከሰሱ ግለሰቦች ውጭ ባለፉት አስር ዓመታት አንድም ከፍተኛ ባለሥልጣን ወይንም ታማኝ በሙስና ተከሶ እስር ቤት አልገባም።

ዘገባውን በሚመለከት የውጭ ጉዳይ ሃላፊው ጆን ኬሪ በሰብአዊ መብቶች መታፈንና በሙስና መካከል ያለውን ቀጥተኛ ግንኙነት አስምሮ ይኼ ጠንቅ የሚያስከትለውን አደጋ ጠቁሟል። **"Corruption is a threat to society at large, not only because of the larceny (robbery) that it embodies in terms of the values and principles that people hope to organize their lives by, but also because of the cynicism it feeds. And that matters because when trust is lost, other more harmful forces always try to fill the vacuum."** አሜሪካ ወዳጅ ያደረገችው የህወሓት/ኢህአዴግ መንግሥት ይኼ ችግር መኖሩን ሲክድ ቆይቷል፤ አሁን ችግሩ ተባብሶ ይፋ ሆኗል። ሆኖም፤ የችግሩ ምንጭ ስርዓቱ መሆኑን አልተቀበለም። የሚከተለው የፖሊሲ ሌሎችን መወንጀል ነው። አጥፊዎች፤ ፀረ-ልማቶችና ፀረ-ሕገ መንግሥት ግለሰቦች፤ ሌቦችና ሙሰኞች ሌሎች ናቸው የሚል ነው። ይኼ ብሂል አስቸጋሪ የሚሆነው የሌለው ግለሰብ ሌባ ሊሆን አይችልም። በአገር ቤት ሆኖ ራሱን ሃብታም ያላደረገ ግለሰብ ምን ወንጀል ሰራ ለማለት ይቻላል? ዋናው የማጥቃት ስልት ተቃዋሚውን ሁሉ በፀረ-ሽብርተኛነት ክስ አሳቦ መቅጣት ለቆይታው ይረዳዋል። ይኼን በሚመለከት ኬሪ የተናገረው አግባብ አለው። **"However, terrorst presence does not give authorities license to use violence indiscriminately."** ጋዜጠኞች፤ ብሎገሮች፤ በሕገ መንግሥቱ መሰረት በሰላም የሚታገሉ ተቃዋሚዎች ሽብርተኞች አይደሉም። ገዢው ፓርቲ እንደ ፈለገ ሽብርተኞች ብሎ ከሶ ያስራቸዋል፤ ያሳድዳቸዋል፤ በድብቅ ይገድላቸዋል፤ ኃብታቸውን ይወርሳል። ዘገባው ከበፊቱ  በበለጠ ግልፅነት ባለው ሁኔታ ስለ ሙስና አድሚነት አንስቷል። ዋናው ነጥብ የፀረ-ሙስና ተቋም መኖሩ ሙስናውን ለመቅረፍ አለመቻሉን ማሳየቱ ነው። **"The law provides criminal penalties for corruption by officials. Despite the government's prosecution of numerous officials for corruption, some officials continued to engage in corrupt practices. Corruption, especially the solicitation of bribes, remained a problem among low-level bureaucrats. Police and judicial corruption also continued to be problems. Some government officials appeared to manipulate the privatization process, and state- and party-owned businesses received preferential access to land leases and credit."** ሕግ ማውጣት ቀላል ነው፤ ማስፈጸም ለሕዝብ ህይወት ደህንነት መቆርቆርን፤ ሃቀኛነትንና ቆራጥነትን ይጠይቃል። ሃላፊነትና ቆራጥነት ከሌለ ተቋም መመስርት ሙስናን አያጠፋም፤ እንዲያውም ሙስናው መዋቅራዊ ሆኖ እንዲደበቅ ያደርጋል፤ ትኩረት የሚያደርገው በዝቅተኛ ሌቦችና ሙሰኞች ላይ ነው።

የአሜሪካኖች ዘገባ በዚህ ፅሁፍ የማቀርበውን ትችት ያጠናክራል። አገዛዙ ለሕዝብ ያልቆመና በሕዝብ የማይዳኝ ስለሆነ ለአመፀኛነት፤ ለኪራይ ሰብሳቢነት፤ ለሽብርተኛነት፤ ለአግላይነት፤ ለስደተኛነት፤ ለአለመረጋጋት፤ ለእርስ በእርስ ግጭት፤ ለተፈናቃይነት፤ ለተገንጣይነትና ለውጭ ሃገሮች ጣልቃ ገብነት ወንፊቶች ፈጥሯል። እነዚህ ችግሮች በተከታታይ ከተከሰቱ ዘላቂነንትና ፍትሃዊነት ያለው

እድገት መሰረት ሊይዝ አይችልም የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ አጠናክራለሁ። በሃያ አንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን በማንኛውም ታዳጊ ሃገር የሚታይና የሚዳሰስ የእድገት ውጤት የሚታየውና ራስን የመቻል አቅም መሰረት የሚይዘው የፖለቲካው አመራር ብሄራዊና ዲሞክራሳዊ ሲሆንና በተቻለ መጠን የሁሉንም ጥቅም ሊያጠናክርና ሊያስተናግድ ሲችል ነው። <u>የፖለቲካው ችግር ካልተፈታ ኪራይ ሰብሳቢነት</u> አይቀረፍም፤ ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ያለው የእድገት መሰረት ለመጣል አይቻልም። ከድርቅ የሚከሰተው ተከታታይ እርሃብ አይወገድም። የፈለገውን ያህል የልማትና የሰብአዊ አገልግሎት እርዳታ ቢጎርፍ፤ እድገቱን በተናጠል ካየነው ማህበራዊ ችግሮች አይፈቱም። በእኔ ግምትም ሆነ በንጥረ ሃሳብ ደረጃ ዓለም ባንክ፤ የልማት ልሂቃንና ሌሎች እንደሚሉት ከሆነ እድገትን ከጠቅላላ የሃገር ገቢና ከጥቂቶች ባለ ፀጋነት በላይ ማየት አስፈላጊ ነው። ለዚህ የሚጠቅሙ አግባብ ያላቸው መስፈርቶች የሚከተሉት ናቸው።

1. መጀመሪያ መሰረታዊ ነጻነቶች---የሰብአዊ መብቶች፤ የመናገር፤ ሃሳብን የመግለጽ፤ የመንቀሳቀስ፤ የመሰብሰብ፤ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ፤ ድርጅት የማቋቋም ወዘተ--መብቶች መከበር

2. ጥሩ ወይንም መልካም አገዛዝ--የሕግ የበላይነት፤ ሚዛናዊ የሆነ የፍርድ አሰጣጥ፤ የግል ኃብት ይዞት መከበር፤ ማንኛውም ዜጋ በማንኛውም ቦታ የመኖርና ኃብት የመያዝ መብት መከበር

3. በየ ደረጃው ሕብረተሰቡን የሚወክል፤ ለሕዝብ ተጠሪነት ያለው መንግሥት (Representative government) ህጋዊ መሆን

4. ሁሉን አሳታፊ፤ አገልጋይና አጎልማሽ የሆነ፤ ሃላፊነት፤ ግልፅነት፤ ፍትሃዊነት ያለው፤ በሞያ የሚመራ ሃገር አቀፍ አስተዳደር (Competency based civil service) መኖር

5. አመቻች የሆነ የአጠቃላይ የፖሊሲ ሁኔታ (Favorable macro policy environment) መኖር

6. በገዢው ፓርቲ፤ መንግሥትና በግል ክፍሉ መካከል የሚኖረውን የኢኮኖሚ፤ የፋይናንስ፤ የገበያ፤ የኢንቬስትመንት፤ የተፈጥሮ ኃብት አጠቃቀም፤ የመደጋገፍ ግንኙነትና ሚና ሚዛናዊ በሆነ መንገድ የሚያስተናግድ አመራርና ደንብ (Synergy and an enabling and empowering regulatory framework) በሕግ መከበር

7. በኢትዮጵያ ዜጎች መካከል የሚኖረውን አስፈላጊና ወሳኝ ማህበራዊ ግንኙነት የሚያጠናክር ራእይና ስራ (Government Commitment to National Political, Economic and Social Cohesion) መተግበር፤ የትምህርት አመራርና ካሪኩለም መተባበርን እንዲያጠናክር ፖሊሲ አውጥቶ መተግበር፤

8. ለሃገር የተፈጥሮ ኃብት፤ ለቅርሶች፤ ለባጀት (እርዳታን ጨምሮ) ለሰራተኛው ሕዝብ አለመባከን የተለየ ትኩረት የመስጠት፤ ጥሪቶችን በሃላፊነት የመጠቀም ሃላፊነት አመራር መኖር

9. ለአካባቢና ለነዋሪዎች ህይወትና ዘላቂነት እንክብካቤና ትኩረት የሚሰጥ መርህ መኖር

10. ለህዝብ አገልግሎት ቅንነትና ችሎታ ያላቸውን ባለሞያዎች ቀጥሮ አግባብ ያለው ደሞዝ መክፈልና

11. የኢትዮጵያን ግዛታዊ አንድነት፤ ብሄራዊ ጥቅም፤ ሉዐላዊነት፤ ደህንነትና ክብር መሰረት አድርጎ ከውጭ መንግሥታት፤

አበዳሪዎች፤ ለጋሶችና ኢንቬስተሮች ጋር የተመጣጠኑ፤ ለሃገር ዘላቂ ጥቅም የሚያስገኙ ውሎችን ማስተናገድ ዋናዎቹ ናቸው።

ከእነዚህ ሁሉ የፖሊሲው አወቃቀር፤ የአገርና የሕዝብ ማእከላዊነት ወሳኝ ነው። ኢትዮጵያ የምትባል ታሪክ፤ እውቅናና ተከታታይነት ያላት አገር አለች ብሎ መቀበል ለዘላቂና ፍትሃዊ እድገት ወሳኝ ነው። የእድገቱ ውጤት ለጥቂቶች አገልግሎት ሳይሆን የአብዛኛውን ሕዝብ ህይወት ለማሻሻል፤ የመካከለኛውን መደብ ቁጥርና ስርጭት ለማስፋፋት፤ ለወጣቱ ትውልድ በተፈለገው መጠን የስራ እድል ለማስፋፋት፤ ለሁሉም ኢትዮጵያዊያን የምግብና ሌሎች ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ አቅርቦቶች በበቂ ደረጃና በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ጥረት ማድረግ አስፈላጊ ነው የሚል መርህ ተከትሎ ተግባራዊ ማድረግ ወሳኝ ነው። “እድገት አለ፤ ዳቦ የለም፤ እድገት አለ መሰረተ ልማቱን ብቻ እዩት፤ እድገት አለ የጥቂት ኃብታቾምች ሚሊየኔርነትንና ኑሮን አይታችሁ ፍረዱ፤ እድገት አለ ብልጭልጩን ከተማ እዩት፤ እድገት አለ ችግሩ የሕዝብ ብዛት ነው፤ እድገት አለ ችግሩ የህዝብ ፍላጎት ለውጥ ነው” የሚሉ የተለያዩ ክፍሎች አሉ። ያም ተባለ ሌላ የማህበረሰብ ችግር እንዳለ አይካድም። የእድገት መርህ በመዋቅራዊ ለውጥ አስገላጊነት--ለምሳሌ ከእርሻ ጋር የተያያዘ የኢንዱስትሪ ልማት፤ የገዢውን ፓርቲ ሞኖፖሊ ለውጦ የግል ክፍሉን ከመስፋፋት ወዘተ ላይ አላተኮረም የምለው ለዚህ ጭምር ነው። በሕዝብ ኑሮ መሻሻል ላይ የተመሰረተ እድገት ጥረቱ

የአብዛኛውን ሕዝብ የፍጆት ፍላጎት ለማሟላት ነው። የሃገር ውስጥ የምርት ኃይሎች እየጨመሩ ሲሄዱ የአብዛኛው የስራ እድል፤ የሕዝብ ገቢ፤ ኑሮና ህይወት ይሻሻላሉ፤ እየተሻሻሉ ሲሄዱ የመግዛት አቅም ይጭምራል ወዘተ። የተያያዙ ናቸው። የኢትዮጵያን እድገት የተለየ ትርጉም እንስጠው የምልበት መሰረታዊ ምክንያት እድገቱ ከአብዛኛው ሕዝብ ህይወት መሻሻል ጋር ግንኙነት ስለሌለው ነው። "እድገት አለ፤ ዳቦ የለም። እድገት አለ ስራ የለም" ወዘተ የድገትን ትርጉም የተለየ አድርጎታል።

በምስራቅ ኤዢያና ፓሲፊክ ሃገሮች አምባገነናዊ አገዛዝም ቢኖር፤ እድገታዊ መንግሥታት የሃገር ወዳድነት ይዘት እንደነበራቸው ብዙ ምርምሮችና ጥናቶች ተደርገዋል። ለዚህ ትኩረት የሰጡ እንደ ቻልመርስ ጆንሶን ያሉ የእድገት ልሂቃንን እጠቅሳለሁ። እድገታዊ መንግሥታት እድገታዊ ነን ሲሉ፤ አመቻች የሆነ ፖሊሲ ይቀርጻሉ፤ ማንኛውም ግለሰብ እንዲሳተፍ ጥረት ያደርጋሉ፤ የተቀነባበረ አገር በቀል ልማት መመሪያቸው ያደርጋሉ፤ ለሴቶች ትምህርትና የስራ እድል ትኩረት ይሰጣሉ፤ የሃገር ውስጥ የግል ተቋሞች እንዲያብቡ ድጎማ ያደርጋሉ፤ ለውጭ እንቬስተሮች አግባብ ያለው መመሪያ ይሰጣሉ፤ በኢጋርነት እንዲሰሩ ጫና ያደርጋሉ፤ ባጀትና እርዳታን ሃገርን ለማጎልመስ እንዲውል ይሞክራሉ፤ የገጠሩ ህዝብ ወደ ከተማ ሲገባ የስራ አማራጭ እድል ይከፍታሉ ወዘተ። በአብዛኛው በፍጥነት ያደጉ ሃገሮች አገር ወዳድና ችሎታ ያላቸው የመንግሥት መሪዎች አሏቸው። እንደ ቻይናና ቬትናም ያሉ በአምባገነን መንግሥታት የሚመሩ እድገታዊ መንግሥታት ከወሓት/ኢህአዴግ አመራር የሚለዩበት ዋና ምክንያት በሃገር ወዳድነታቸው ነው። ጠባብ ጎሰኝነትና ኪራይ ሰብሳቢነት ጠባብ የሆነ የኢኮኖሚ ቤት ይሰራል። ጠባብ ቤት የፈጠረ ባለቤት ሁሉም ተሳትፎ የስራ እድሉንና የማምረት ኃይሉን መሰረት ሊያጠናክርና ሊያሰፋ አይችልም። የአሁኑ በኪራይ ሰብሳቢነት የተበከለ አገዛዝ የእድገቱ ሞተር ራሱ ሆኖ የሚያገኘውን የእርዳታ ቤንዚን ለራሱ ይጠቀማል፤ ውጤቱን ለራሱ ያደርጋል። የጠበበ የእድገት መርህ የጠበበ ውጤት የሚኖረው ለዚህ ነው።

በዛሬይቱ ኢትዮጵያ ኪራይ ሰብሳቢዎችን፤ ባለሥልጣናትን፤ የኢኮኖሚ አንቀሳቃሾችን፤ የጎሳ ልሂቃንን፤ ገዢውን ፓርቲ፤ የፈጠራቸውን ተቋሞችና በበላይነት የሚያዝባቸውን የመንግሥት ተቋሞች ለመለየት አይቻልም። የተሳሰሩ ናቸው። ፓርቲው፤ በተለይ ህወሓት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ተሳታፊና አትራፊ ሆኗል። ነጋዴ ነው። ሃገሪቱን የሚያስተዳድሩት ግለሰቦች የሚመረጡትና የሚሾሙት በችሎታ አይደለም። በፓርቲና በጎሳ ታማኝነት ነው። አንዳንድ መስሪያ ቤቶች ከተላላኪ ጀምሮ እስከ ስራ አስኪያሃጅ የአንድ ብሄረሰብ አባላት ናቸው። አይን ያወጣ የጎሳ አድልዎ ይታያል። አስተዳደሩና አመራሩ ከመስራቅ ኤዢያ፤ ቻይናንና ቬትናምን ጨምሮ ይለያል፤ ቻይና ችሎታ ላላቸው ግለሰቦች ቅድሚያ ትሰጣለች። ለምሳሌ፤ በዓለም ባንክ ዋና ኢኮኖሚስት ሆኖ ያገለገለው ሊን በችሎታው ተመርጦ ነው። ሳነጋግረው በቻይና የኮሙኒስት አመራሩ መመሪያ ሃገሪቱን ለማስተዳደር ብቃት ያላቸው ቢቻል ኮሙኒስት የሆኑ ካልተቻለ ሃገራቸውን የሚወዱና ችሎታ ያላቸው በዓለም ደረጃ ተወዳዳሪነት ያላቸው እንደሆኑ ነግሮኛል። ልንክደው የማንችለው አበይት ክስተት በኢትዮጵያ ችሎታ የሌለው (Incompetent) የአንድ ብሄረሰብ አባል በቋንቋው ብቻ ተለይቶና ተመርጦ ችሎታ ያላቸውን ኢትዮጵያዊያን ያዛል፤ ይመራል፤ ከስራ ያባርራል። በምትካቸው የራሱን የጎሳ አባል ያስገባል። ተራ ሾፌር በጀርባ ሆኖ ሞያ ያለውን ሌላ ግለሰብ ይከታተላል፤ ያዛል። በሌሎች ኢትዮጵያዊያን ላይ እምነት ስለሌለ እያንዳንዱ የመንግሥት መስሪያ ቤት ተከታታይ ወይንም ተቆጣጣሪ የሆነ የአንድ ብሄረሰብ ተወላጅ ባልደረባ አለው። እነዚህ ግለሰቦች በጎሳቸውና በቋንቋቸው ሳይሆን ከሌላው ጋር ተወዳድረው በሞያቸው ብቻ ሃገራቸውን ቢያገለግሉ የሃገር ሸክም አይሆኑም ነበር። ጥላቻን አይፈጥሩም ነበር። በደሉ በጎሳ ስርጭት ብቻ አይደለም። የመንግሥት አገልግሎት መበደሉና መበከሉ ከፍተኛ ዋጋ እየተከፈለበት ነው። ዋጋውን የሚከፍለው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አመራር ሆነ የእድገትና የምርት ውጤት የገዢው ፓርቲ ባለ ሥልጣናት የፖለቲካ ውሳኔ ነው። የሚያስታውሰኝ የፈረሰውን የሶቪየት ህብረት የኢኮኖሚ አመራር ነው። ትእዛዙ "ይኼን ያህል አምርተናል" የሚል ዘገባ አቅርቡ ነው። የኢትዮጵያን እጥፍ እድገት ከጥያቄ ውስጥ ያስገባው ይኼ የፈጠራ ማስረጃ ልምድ ስለሆነ ነው። የእርሻ ምርት አደገ ሲባል የፖለቲካ ውሳኔ ነው። የግብርና ስራ "ሚሊየኔሮች አሉ" ሲባልና በቴሌቪዢን ቀርበው ምስክርነት እንዲሰጡ ሲደረግ የፖለቲካ ውሳኔ ነው። አንዲት ዘመዴ ለጉብኝት አሜሪካ መጥታ የነገረችኝ አይረሳኝም። አንድ የጎንደር ወጣትና ተናጋሪ ገበሬ መንግሥት አባብሎት፤ መደጎሚያ ሰጥቶት (አዲስ ልብስና ጫማ፤ መጓጓዣ ወዘተ) አዲስ አበባ እንዲመጣ ይደረጋል። በዚህ መንግሥት ኃብታም መሆኑን በቴሌቪዢንና ሬዲዮ እንዲናገር ከተደረገ በኋላ ተመልሶ ይሄዳል። ዜናውን የሰሙ ቤተሰቦቹና የአካባቢው ሕዝብ "ምን ሰጡህ፤ አሁን ኃብታም ስለሆንክ ዘመዶችህን ሁሉ ለመርዳት ትችላለህ" ወዘተ አሉት። አፍሮና ደንግጦ "እኔ ከሰጡኝ ልብስና ጫማ በስተቀር ሌላ ምንም አልሰጡኝም። ለምን እንደሆነ የጠሩኝ አልገባኝም፤ ምነው እምቢ ባልኩኝ" አለ ይባላል።

"ለምን ውሸት ተናገርክ፤ እኛን አሳፈርከን እኮ" ሲሉት "እምቢ ብል ችግር እንደሚደርስብኝ ስለገመትኩ ነው" አለ። ቁም ነገሩ የፈጠራ ማስረጃ የተለመደ መሆኑ ነው። እጥፍ ድርብ የእርሻ እድገት አለ የተባለውን የፈጠራ ወሬ አንድ የዓለም ባንክ ኢኮኖሚስት "ሃሰት ነው" ብሏል። የዚህ መስፈርት አሁን በድርቅ ረሃብ የሚሰቃየው ብዙ ሚሊየን ሕዝብ ነው።

## የድርቅ እርሃብ ስርዓት ወለድ ነው

የኢትዮጵያ ዘላቂነትና ፍትሃዊ እድገት ዋስትና የሚኖረው አገራችን ያላትን የተፈጥሮና የሰው ኃይል ጥሪቶች፤ ገንዘብና ሌሎች ግብዓቶች አጋባብና ሃላፊነት ባለው መልክ ለመጠቀም ስትችል ነው። የእድገት መሰረታዊ ዓላማ ራስን ለመቻልና ከተከታታይ የውጭ እርዳታ ነጻ ለመሆን፤ አገር በቀል ኢኮኖሚ ድህነትን ቀርፎ ተወዳዳሪነት እንዲኖረው ለማድረግና ብሄራዊ ነጻነት፤ ክብርና ሉዐላዊነት አስተማማኝ እንዲሆኑ ለማድረግ ነው። እድገት በተናጠል እነዚህን ግቦች ሳያሟላ ሊከናወን ይችላል፤ አሁን እንደሚሆነው ማለት ነው። እኔን ያሳሰበኝ  ግዙፍ የሰው እምቅ ኃብት፤ የተፈጥሮና የገንዘብ ኃብት መባከኑ ነው። እርግጥ፤  እድገት አለ ቢባል ተቀባይነት አለው። ሆኖም በተከታታይ እጥፍ ድርብ እድገት አለ ሲባል የፖለቲካ ውሳኔ እንጅ የማህበረሰብ ህይዎት መሻሻሉን አያሳይም።

ለምሳሌ፤ ኢትዮጵያ ከዓለም ሃገሮች በተከታታይ የምግብ ጥገኝነትን አንደኛ ደረጃ የያዘች መሆኑን መንግሥት ይከዳል። በFAO ግምት ከ2010-2050 ኢትዮጵያ የምግብ ምርቷን ሰባ በመቶ ማሳደግ ይኖርባታል፤ መንግሥት ይኼን አይቀበልም። The 2011 World Hunger Index በእርሻ ልማት ላይ የተመሰረተው የኢንዱስትሪ ልማት መርህ ውጤት አሳይቶ እንደሆነ ለማወቅ ባካሄደው ምርምምር እንዲህ ብሏል። “ኢትዮጵያ አሁንም ረሃብተኛ ከሆኑ ሃገሮች መካከል የመጀመሪያውን ደረጃ ይዛለች።” በተከታታይ የእድገት አመታት የምግብ ሸማች ሆና ቆይታለች። የዛሬ አራት አመት 700,000 ቶን ስንዴና ሌላ የምግብ እህል <u>አንድ ቢሊየን ስምንት መቶ ሽህ ዶላር</u> አውጥታ ገዝታለች። የዋጋ ግሽበትን አድካሚነትን ለማጤን የምርት ውጤት ዝቅተኛ መሆኑን መቀበል ግድ ይላል።  ካድሬዎች የፖለቲካ መርህ ተከትለው በእየ ዓመቱ የእርሻ እድገት ካለፈው ተሻሽሏል እያሉ የፈጠራ ማስረጃ በማቅረባቸው አመኔታን አጥተዋል። በእኔ ግምት የገጠሩ እርሻ ውጤት አድጓል ለማለት ለሕዝቡ የሚደርሰውን የእርሻ ውጤት አቅርቦትና የሚዘገንን ረሃብን ከማየት የበለጠ መስፈርት ሊኖር አይችልም። ስቴፋን ዴርኮንና ዳንኤል አስፋው ስለ ገጠሩ እድገት ጉዳይ ያሉትን እጠቅሳለሁ “Whether from the perspective of income, health or education, poverty levels are of grave concern for Ethiopia.” የዓለም ባንክንና የአሜሪካ መንግሥትን እጅ እየጠበቁ መኖር የእድገት መለኪያ ሊሆን አይችልም። <u>ሁል ጊዜ ድህነትንና ረሃብን</u> ተጠቅሞ ልመናን መፍትሄ የሚያደርግ አመራር <u>ክብረ-ቢስ ነው።</u> የመረጃ ታማኝነት የሌለው ውጤት ማሳየት የሃፍረት ገጽታ ሆኗል። ዛሬ ብዙ ተመልካቾች የሚሉት “በደርግ መንግሥት ሶስት ምግብ ለመብላት የሚችለው ሕዝብ ሁለት ምግብ ለመብላት አይችልም” ነው። ይኼ አባባል ከሰብአዊ/ማህበረሰባዊና ከኢኮኖሚ መብቶች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው። ይኼን የሚያጠናክሩ ሌሎች ዓለም አቀፍ ድርጅቶችና ምርጥ ልሂቃን ያወጧቸው መረጃዎች አሉ። ጥቂቶቹ።

Foreign Policy Failed States Index, 2011. የወደቁ ወይንም የመውደቅ አዝማሚያ የሚያሳዩ ሃገሮች ምን ምልክቶች ያሳያሉ? የሰብአዊ መብቶች መረገጥ፤ የዜጎች መሰደድ፤ የፖለቲካና የጎሳ አድልዎ፤ የመንግሥት ተቀባይነት መናድ፤ ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙስና፤ የተዛባ ገቢና እድገት፤ የሕዝብ ክፍሎች መገለል፤ አቤቱታ መፍትሄ አለማግኘት፤ የልሂቃን እርስ በእርስ ግጭት፤ የኃብት ሽሚያና የእድገት ተከታታይነት አለመኖር ይገኙበታል። በዚህ መስፈርት <u>ኢትዮጵያ ከስድሳ ሃገሮች ሃያኛውን ደረጃ ይዛለች።</u> የሃገር መፈራረስና የእርስ በእርስ ግጭት ሊከሰት ይችላል የሚለው አግባብ አለው የሚለውን አመለካከት ያጠናክራል--IFPRI, Global Hunger Index, 2011. ኢፍፕሪ በእርሻ ልማት ፖሊሲ ጥናት ከፍተኛ ደረጃ የያዘ ድርጅት ነው። ባደረገው ጥናት <u>ከመቶ ሃያ አንድ ሃገሮች መካከል ኢትዮጵያና</u> ሌሎች አራት ሃገሮች የመጨረሻ ፍፁም ድሃ እንደሆኑ ያሳያል፤ በእነዚህ ሃገሮች ረሃብተኛነት “ወደሚዘገንን ደረጃ ደርሷል” ይላል፤ መጥፎ የአየር ሁኔታ ቢከሰት ብዙ ኢትዮጵያዊያን ሊያልቁ ይችላሉ። አሁንም እያለቁ ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ ለምግብ ዋስትና ትኩረት ኣለመስጠቱ መሰረታዊ የፖሊሲ ግድፈት ጥያቄ ሆኗል። ከላይ የቀረበው ጥናት ለዚህ ወቅታዊ ችግር ለምን ትኩረት እንዳልሰጠው አስገርሞኛል።

Legatum Prosperity Index 2011. አንድ ሃገር እያደገ ሲሄድ የነፈስ ወከፍ ገቢ ያድጋል፤ ኑሮ ይሻሻላል፤ ድሃ የነበረው የእኔ ነው <u>የሚለው ሃብት ይኖረዋል። በዚህ መስፈርት ኢትዮጵያ ከአንድ መቶ አስር ሃገሮች መካከል ዝቅተኛ የሆነውን አምስተኛ ደረጃ ተቀዳጅታለች። በኢኮኖሚና በግለሰብ ነጻነት፤ በማህበረሰብ ካፒታል አጠቃቅምና መባከን፤ አግባብ ባለው የእድል መስክ ክፍተትና በጤናማነት ከመቶ አስር ሃገሮች መቶ ሰባተኛ ሆናለች፤ በታች ያሉት ሶስት ሃገሮች</u> ናቸው።  Oxford Univerisy Mutidimensional Poverty Index, 2011/2012 ስናይ የእድገት መርህ በሕዝብ ህይወትና ኑሮ መሻሻል መሰረት የሚካሄድ ሲሆን ድህነት ሙሉ በሙሉ ባይቀረፍም መጠኑ፤ ስፋቱና ጥልቀቱ ይቀንሳል የሚል ግንዛቤ ይሰጠናል። የገቢና የኃብት ስርጭት ሚዛናዊ ይሆናል። ትምህርትና የጤና አገልግሎት ጥራት ይኖረዋል፤ የዜጎች ኑሮ ይሻሻላል፤ የሚሻሻልበት መሰረት ይጣላል። በዚህ መስፈርት <u>አርባ አምስት በመቶ</u> የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀን የሚያገኘው (በአማካይ) <u>ገቢ ከአንድ ዶላር ሃያ አምስት ሳንቲም በታች</u> ነው። ዓለም ባንክ በቅርቡ ያወጣው <u>ዘገባ ሰላሳ ሰባት ሚሊየን</u> ወይንም ከአንድ ሶስተኛው በላይ ድሃ ወይንም ፍጹም ድሃ ነው። World Bank, Ease of Doing Business Index 2011ን ስናይ የማህበረሰቡ ህይወት አደገኛ ደረጃ ላይ ደርሷል ወደሚል ድምዳሜ እንደርሳለን።  በዓለም ደረጃ <u>ሲታይ፤ ዘጠና</u>

በመቶ የሚሆነውን የስራ እድል የሚፈጥረው የግሉ ክፍል ነው። የግል ክፍሉ የሚያብበው የግል ኃብት የሕግ ዋስትና ሲኖረው፤ መሬት፤ ብድር፤ ፈቃድ ያለምንም ተፅእኖና አድልዎ ሲስተናገድ፤ ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ጉቦና ሙስና ወንጀል ሲሆኑ፤ ባለስልጣናት ሚዛናዊ ሲሆኑ፤ ደንቡና ህጉ ለግል ክፍሉ ድጋፍ የሚሰጥ ሲሆን ነው። በዚህ መስፈርት ኢትዮጵያ፤ በብድር በኩል ከመቶ ሰማንያ ሰባት ሃገሮች መቶ ሃያ ስምንተኛ፤ በግል ኃብት አስተማማኝነት ከእነዚህ ሃገሮች መቶ ዘጠኝኛ ናት። አንድ ግለሰብ የግል ተቋሙን ለማስመዝገብ ይንገላታል፤ ጉቦ እንዲከፍል ይገደዳል። ዛሬ የሚኖሩበት ቤት ፈርሶ መሬታቸው የሚነጠቀው ኢትዮጵያዊያን ብዛት በየትም አገር ታይቶ የማይታወቅ ሆኗል። ከላይ በጠቀስኩት መስፈርት ፈጣን እድገት ታሳያለች የምትባለው ኢትዮጵያ ከመቶ ሰማንያ ሰባት ሃገሮች መቶ ዘጠኝኛ ደረጃ የያዘችው ለዚህ ነው።

ነጻነት ከሌለ ፍትሃዊ እድገት አይታሰብም

ጥናቱ ያላነሳው መሰረታዊው ጉዳይ የፖለቲካውን ሁኔታ ነው። መንግሥት የመሰለውን ቡድን መሰየሙ ያመጣው ውጤት ነው የሚሉ ታዛቢዎች አሉ፤ አግባብ አላቸው። The Heritage Foundation and Freedom House Indices on Economic and other Freedoms, 2011-2014 እንመልከት። ነጻነት የሌለው ሕዝብ ለመብቱ ለመከራከር አይችልም፤ ካልቻለ ጥቅሙን ለማስከበር ያስቸግረዋል። ፍርድ ቤቶች የገዢው ፓርቲ ተቀጥላ መሆናቸው የግሉ ክፍል ችግር ሲደርስበት ፍትህ አያገኝም። የኮንትራት ችግሮች ሲከሰቱ ውሳኔው የፖለቲካ ይሆናል። ለምሳሌ፤ አንድ ግለሰብ ከባንክ ተበድሮ የሚሰራው ፎቅ በተወሰነው ጊዜ ባያልቅ ወይንም የሚገዛው ብረታ ብረት ወይንም ስሚንቶ ዋጋ ከገመተው በላይ ቢጨምር ህንጻውን እንዲያስረክብ ይገደዳል፤ ሲገደድ ብልጣ ብልጥ በዝቅተኛ ዋጋ ከባንኩ ይገዛዋል። ከባለሥልጣናት ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ያለው ግለሰብ ብዙ መሬት ገዝቶ ህንጻ ያልሰራበትን አትርፎ ይሸጣል። ባለሥልጣን ወይንም ከባለሥልጣን ጋር የጥቅም ቁርኝት ያለው ግለሰብ ችግር ሲደርስበት ጊዜ ይሰጠዋል። ይኼ አሰራር የተለመደ ሆኗል። በራሱ ጥረት ተደራድሮ ለሚሰራው ዜጋ ብድሩን እንደ ገና ለመዋዋል የሚያስችል መመሪያ የለም። ባንኮቹ የህወሓት/ኢህአዴግ መገልገያ ስለሆኑ የግል ብድር አስተማማኝ አይደለም፤ ፓርቲው በፈለገ ጊዜ በቀረጥ፤ በፈቃድ፤ በጥራት ወዘተ ጣልቃ ሊገባ ይችላል። በተመሳሳይ Freedom House, World Freedom Index 2014 የሚለውን ዘገባ ላሳይ። "ኢትዮጲያ በከፊል ነጻ ከሆኑ ሃገሮች ተባብሳ ዛሬ ነጻ ካልሆኑ ሃገሮች መካከል አንዷ ሆናለች።" ይኼ ዘገባ Human Rights Watch, the Committee to Protect Journalists (CPJ), Amnesty International, the U.S. Department of State ካወጡት ዘገባ አይለይም። እነዚህ ዘገባዎች የሚጋሩት አስኳል ጉዳይ በሰብአዊ መብቶች አለመከበርና በገቢና ሃብት ስርጭት መዛባት መካከል ያለውን ግንኙነት ጭምር ነው። በተለይ ሂውማን ራይትስ ወች በተደጋጋሚ ያቀረበው ማስረጃ የውጭ እርዳታ ከሰብአዊ መብቶች መገፈፍ ጋር ቀጥታ የሆነ ግንኙነት እንዳለው ያሳያል። "Sustainable and inclusive development is possible only where human rights of all individuals, particularly young women and girls are respected, protected and fulfilled." በዘላቂና ፍትሃዊ ልማት ስኬታማነትና በሰብአዊ መብቶች መከበር መካከል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለ። ይኼን በኢትዮጵያ ማነቆ የሆነ ችግር ለመፍታት ካልተቻለ ዘላቂና ፍትሃዊ እድገት አይኖርም። ምክንያቱም፤ በእድገቱ ለመሳተፍና ለመገልገል ያልቻለ ወጣትና ሌላ ሕዝብ የሚኖረው ምርጫ ከሃገር መሰደድ ወይንም ለዚህ ያበቃውን አገዛዝ ታግሎ መለወጥ ነው። ከሃገር ለመሰደድና ስራ ለማግኘት ተቀባይ ያስፈልጋል፤ ተቀባዮች አንችልም ከሚሉበት ደረጃ ደርሰናል። ህወሓት/ኢህአዴግ የስራ እድል እጥረትን በስደተኛነት ስልት የሚወጣበት ጊዜ እያለፈ ሂዷል ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሻለሁ።

የMo-Ibrahim African Governance Index 2010 እና ተከታታይ ዘገባዎች ያተኮሩት በሕግ የበላይነት፤ በሰብአዊ መብቶች መከበርና በሕዝብ ተሳታፊነት፤ በማህበረሰብ እድገት ዘላቂነትና ፍትሃዊነት ባለው እድገት ላይ ነው። ኢትዮጵያ በሁሉም መስፈርቶች ዝቅተኛ እርከን እንደያዘች ነው። UNDP National Human Development Report, Ethiopia, 2014 እና Human Development Index 2014 አጠቃላይ የሆነ ስእል ይሰጡናል። ህወሓት/ኢህአዴግ ባይቀበለውም በሰብአዊ እድገት በኩል ኢትዮጵያ በተከታታይ ዝቅተኛ ደረጃ አሳይታለች። "Ethiopia's HDI and its relative ranking have not moved appreciably during the past decade," 173rd out of 187 countries covered. በአንደኛ ደረጃ ትምኅርት ስርጭት አገር አቀፍ ነው ባይባልም፤ ከፍተኛ ውጤት አሳይታለች፤ በሌሎቹ መስፈርቶች አሁንም ዝቅተኛ ናት። በጤና አገልግሎት ጥራት ዝቅተኛ፤ በእናቶች የወሊድ አገልግሎት ዝቅተኛ፤ በመፀዳጃ ዝቅተኛ፤ ረሃብን በመቅረፍ ዝቅተኛ፤ በነፍስ ወከፍ ገቢ ዝቅተኛ ወዘተ ናት። የእኔን ዘገባ ወደ ጎን እንተወው። እድገት ባሳየችው ከተማ በአዲስ አበባ ዘጠና በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ዘመናዊ መፀዳጃ የለውም። CIA፤ ዓለም ባንክና እና ይኼ ዘገባ የተስማሙበት 39 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በቀን የሚያገኘው የነፍስ ወከፍ ገቢ ዓለም ባንክ ለኑሮ ያስፈልጋል ከሚለው ከሁለት የአሜሪካን ዶላር በታች፤ ማለትም አንድ ዶላር ከሃያ አምስት ሳንቲም ነው። ኢትዮጵያ ፍጹም ድሃ ከሚባሉት ሃገሮች መካከል አንዷ ናት፤ በዓመት የሚገመተው የነፍስ ወከፍ ገቢ $470 ከሳሃራ በታች ከሚገኙ ሃገሮች አንድ ሶስተኛ፤ ቢበዛ ግማሽ ነው። ድሃው ብቻ ሳይሆን፤ ገቢያቸው ከፍተኛ ነው ተብሎ የሚነገርላቸው ኢትዮጵያዊያን በኑሮ ውድነት እንደሚማረሩ የአደባባይ ምስጢር ነው። ዩኤንዲፒና አንክታድ ባወጡት ዘገባ እንደተረዳሁ ፈጣን እድገት ያሳየችው ኢትዮጵያ የማህበረሰቡን ፍላጎት ለማሟላትና የኢኮኖሚውን መዋቅር ለመለወጥ አልቻለችም። የግሉን ክፍል አፍናለች፤ አላፈነችም ቢባል አላፋፋችም። "የኢትዮጵያ መንግሥት የተለየ ትኩረት ለግል ክፍሉና ለኢንዱስትሪ ልማት መስጠት አለበት። የትምህርት ይዘቱ ለስራ ለሚረዱ የቴክኒካል ስልጣኔ ትኩረት መስጠት አለበት። የብድር አቅርቦትና አጠቃቀም መሻሻል አለበት። የኢኮኖሚው መዋቅር በፍጥነት መቀየር አለበት።"

UNCTAD እና UNDP የሚስማሙበት መሰረታዊ የፖሊሲ ጉዳይ አለ፤ ይኼውም እድገት ቢኖርም የኢኮኖሚው መዋቅር አሁንም አልተለወጠም የሚል ነው። **"Ethiopia has yet to undergo the kinds of structural changes needed to sustain the pace of economic growth and to <u>make it more equitable</u>."** ይኼን ለማድረግ በቁጠባ የሚገኘው ካፒታል ማደግ አለበት። መንግሥስት ታክስ ለመሰብሰብ ካልቻለ ይኼ ግብ ስኬታማ አይሆንም። ለፍጆት የሚወጣው ግዙፍ ገንዘብ መቀነስ አለበት። የእድገቱ ውጤት ፍትሃዊ መሆን አለበት። ለፍጆት የሚወጣው ከጠቅላላው <u>የሃገሪቱ ገቢ ሰባ አምስት በመቶ</u> ነው። ለቁጠባና ኢንቬስትመንት የሚቀረው ገንዘብ ከየት እንደሚመጣ ለማወቅ አልቻልኩም። ቁም ነገሩ የኢኮኖሚው መዋቅር መለወጥ አለበት የሚለው ነው። መዋቅር የሚለወጠው ፖሊሲው ሲለወጥ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት የልማት ባጀቱን በተከታታይ የሚያሟላው በውጭ እርዳታ ነው፤ <u>በአማካይ፤ አምሳ በመቶ</u> የሚሆነው ድጋፍ በብድርና በእርዳታ የሚገኝ ነው። ይኼ ዘላቂነት የለውም። ይኼም እራሱ መዋቅራዊ ሆኗል።

ስለመዋቅራዊ ለውጥ አስፈላጊነት አንክታድ ያቀረበው ትንተናና ትችት አግባብ አለው። **UNCTAD, Most of the World's poorest nations stuck in a structural rut," December 2014** የሚነግረን ኢትዮጵያ ስርዓት ወለድ ከሆነ አሮንቃ (አዘቅት) ከገቡት ሃገሮች መካከል አንዷ መሆኗን ነው። **"The planet's poorest nations, like Ethiopia, Malawi and Angola have failed to cash in on strong economic growth due to a <u>lack of structural reforms</u> and left them wallowing in poverty," said AFP quoting UNCTAD. "The LDC paradox arises fromn the failure of LDC economies to achieve structural changes despite having grown vigorously as a result of strong export prices (Angola), and rising aid flows (Ethiopia)."** የኢትዮጵያ ፈጣን እድገት የውጭ እርዳታ ውጤት መሆኑን ያረጋግጣል። በውጭ እርዳታ ሆነ በውጭ ንግድ የሚገኝ ገቢ ብቻውን ድህነትን አያጠፋም፤ በተለይ ግዙፍ ኃብት በኪራይ ሰብሳቢዎች ከተነጠቀ። መዋቅሩን ለመለወጥ የፖሊሲውን ትኩረት መለወጥ ያስፈልጋል። የፖሊሲውን ለውጥ ስኬታማ ለማድረግ የፖለቲካውን አመራር መለወጥ ያስፈልጋል። አለያ፤ <u>ከማንወጣው "አዙሪኝ/ዑደት"</u> ውስጥ እንገባለን **(Vicious cycle).** የኑሮ ውጣ ውረድ የዚህ ውጤት ጭምር ነው። መዋቅሩን ለመለወጥ በመንግሥትና ፓርቲ ባለሥልጣናት ደረጃ የሚካሄደው ግልፅ ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ዘረፋ፤ ጉቦ፤ ሙስናና ከሃገር የሚሸሸው ሃብት መቆም አለበት። ጥናቱ ይኼን ሃቅ ወደ ጎን ትቶታል።

የተቆላለፈ የአድልዎና የደላላዎች የበላይነት ማነቆነትና አጥፊነት

በሌላ በማስረጃ ሰንጠረዢ የተደገፈ ሃተታ እንደማሳየው ገዢው ፓርቲ ህወሓት ለይስሙላና በክልል ደረጃ ደጋፊዎችን ለማፍራት "ዲሞክራሳዊ" አገዛዝ እንዳለ ለማስመሰል የክልል ኃብታሞች ፈጥሯል። ገዢውን ፓርቲ በበላይነት የሚያሽከረክረው ህወሓት የፖለቲካውን ስልጣን ከማረከ በኋላ የዘመናዊ ኢኮኖሚ አውታሮችና የተፈጥሮ ኃብትን በሃገር ደረጃ ማርኳል። ስለዚህ የኢትዮጵያ የፖለቲካና የኢኮኖሚ የበላይ ባለቤት ህወሓት ነው የሚሉ ታዛቢዎች አግባብ አላቸው። ይኼ ባለቤትነት የኢኮኖሚ ጥቅሙ በግልፅ ይታያል። የጥቂት አባላትንና ደጋፊዎችን ገቢና ኃብት ለማሳደግ እረድቷል። በየደረጃው ጉቦ፤ ጎሳዊ አድልዎ፤ ሙስናና ከሃገር የሚሸሽ ግዙፍ ዘረፋና የድብቅ ሽሸት እንዲከሰት እየተደረገ ነው። የውጭ ኢንቬስተሮች ለህወሓት አባላትና ደጋፊዎች ጠቃሚነት ስላላቸው ከሃገር ውስጥ ኢንቬስተሮች የበለጠ እንክብካቤ ይደረግላቸዋል። በድምሩ ሲታይ ኢኮኖሚው ያለምንም ተፅእኖ በመወዳደር ሊሰራ አልቻለም። የፖለቲካ ምርኮውን ወደ ጎን ትተን በሃገሪቱ ሉዐላዊነት፤ በኢኮኖሚውና በማህበረሰብ ህይወት ላይ ያስከተለውን ጫናና በደል ሳንስለች እንይ። **Reporter** የተባለው የህወሓት ደጋፊ ጋዜጣ ከመለስ እልፈት በፊት እንዲህ ብሎ ነበር። ከሃገሪቱ የሕግ ገበያ ጋር ተወዳዳሪ "የሆነ የጥቁር ገበያ ተስፋፍቷል፤ መንግሥት ሊቆጣጠረው አልቻለም።" ያልቻለበት ዋና ምክንያት የፓርቲና መንግሥት ባለስልጣናት፤ በተለይ፤ የስለላ፤ የመከላከያ፤ የፌደራል ፖሊስና ሌላ ኃይሉ እጅ ስላለበት፤ በማጭበርበር የሚሰራው ነጋዴ የሚፍጨረጨረው በአጭር ጊዜ ትርፍ በማግኘት ዙሪያ በመሆኑ ጭምር ነው።

መለስ የዋጋ ግሽበትንና የኃብት ሽሸትን አስመልክቶ ያለውንም ሪፖርተር አብሮ አቅርቦት ነበር። "የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ክፍል ለውጭ ኢንቬስተሮች ክፍት እየሆነ ሂዷል፤ እኛ ካልተጠነቀቅን፤ ከእጃችን ወጥቶ ሃገራችንም የማጣት አደጋ ይታያል።" ዛሬ ቁልፍ የሆኑትን የኢንዱስትሪ ክፍሎች የሚቆጣጠሩት የውጭ ኢንቬስተሮች ናቸው። አደጋው ተነገረ እንጅ የፖሊሲ ለውጥ አልተደረገም። በዚያ ጊዜ <u>የሸሸው ሁለት ቢሊየን ዶላር</u> እንዲመለስ ጫና አልተደረገም። ሕዝቡ መንግሥትን የማያምንበት ምክንያት <u>ይኼው ነው። ገንዘቡን ያሸሹት ወንጀለኞች የገዢውን ፓርቲ አባላት ያካትታል። በተጨማሪ፤ በወቅቱ፤ መንግሥት በግሉ ክፍል የጫነው ሰላሳ አምስት በመቶ</u> የሚሆን ቀረጥ ለግል ክፍሉ ማነቆ መሆኑን **Index of Economic Freedom, 2010/2011 "prohibitive and beyond repair"** በሚል ዘገባ አሳይቶ ነበር:: ቫትም ሆነ ሌላ ቀረጥ የሚከፍለው የተወሰነ ክፍል ነው። አብዛኛውን ኢኮኖሚ የሚያንቀሳቅሰው ክፍል ከታክስና ቀረጥ ውጭ ነው። በተመሳሳይ፤ ከሃገር የሚሸሸውን ግዙፍ ሃብት በሚመለከት **Global Financial Integrity** ኢትዮጵያ **$11.7 billon** ተሰርቆ እንደሸሸባት አሳይቶ "የኢትዮጵያ ሕዝብ እየደማ ነው" የሚል ማሳሰቢያ አቅርቦ ነበር።

በቅርቡ የቀድሞው የደቡብ አፍሪካ ፕሬዝደንት እምቤኪ የመራው ጥናት ያሳየው ዘገባ ኢትዮጵያ ከሃገር እንደጎርፍ ከሚሸሸባቸው አስር ሃገሮች መካከለ አንዷ መሆኗን አስመስክሮ ባለፉት አራት አመታት ብቻ አስር ቢሊየን ዶላር እንደተሰረቀች ተናግሯል፤ በዓመት ለልማት ያገኘችው አንድ አራተኛ መሆኑ ነው። ይኼ ድርጅታዊና ማፊያዊ የሚመስል ዘረፋ እንዴት እንደሚካሄድ ሕዝብ መወያየት አለበት። ጥናቱ ይኼን ፈጽሞ አልነካውም።

**Reporter July 24, 2011** አልቀመስ ያለውን የዋጋ ግሽበት አስመልክቶ መንግሥትን ሲተች እንዲህ ብሏል። "ብዙ የርካሽ ብር ጥቂት የአቅርቦት እቃዎችን ያባርራል፤ አገር ቤት የሚመረተው ከፍላጎት ጋር አልተመጣጠነም። በዚህ ዓመት በአንድ ቀን ብቻ ዋጋ አምሳ በመቶ ጨምሯል። ስደተኛው የሚልከው ገንዘብ የዋጋውን ግሽበት አባብሶታል። ገበሬው በፖሊሲው ተወጥሯል፤ ገቢው ከፍ ብሏል ቢባልም የሚፈልገውን ለመግዛት አልቻለም። እድገቱ ሚዛናዊ አለመሆኑ በየቦታው ይታያል።" ኢኮኖሚውን እንቆቅልሽ የሚያስብለው የአገር ውስጥ የፍጆት ኢንዱስትሪ አለመስፋፋቱ ብቻ አይደለም። ተራው ሕዝብ የሚሸምተው በአገር የሚመረተውን ስለሆነ፤ መንግሥት ለሃገር ኢንዱስትሪ መስፋፋት ትኩረት አልመስጠቱ ለዋጋው ግሽበት መጋቢ ሆኗል። ለምሳሌ፤ ኢትዮጵያ ሰሊጥ ሸጣ የምግብ ዘይት በውጭ ምንዛሬ ትገዛለች። ገዢው ፓርቲ አላሙዲ በዓመት አንድ ሚሊየን ቶን ሩዝ ለሳውዲ ገበያ እንዲያቀርብ ለም መሬትና ወንዝ ሰጥቶ የተራበውን የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመመገብ በውጭ ምንዛሬ ስንዴና ሌላ ጥራ ጥሬ ይሸምታል። አሜሪካኖች ረሃቡ ሌላ አደጋ እንዳያስከትል የምግብ እርዳታቸውን ይቸራሉ። የእርሻ ምርት ኃይሉን፤ በተለይ ዝቅተኛ አምራቹን ደጉመው ዘላቂ መፍትሄ አልፈጠሩም።

ኪራይ ሰብሳቢነት ስር ሰዷል

ዛሬ በመንግሥትና ፓርቲ ባለሥልጣናት ደረጃ የሚካሄደው ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ጉቦ፤ ጎሳዊ አድልዎ፤ ሙስናና ከሃገር የሚሸሽ ሃብት ለኢትዮጵያ ደህንነትና ዘላቂነት፤ ለመላው ሕዝቧ ኑሮ መሻሻል ከፍተኛ አደጋ እያስከተለ ነው። ስለ አገዛዝ ስርዓት ሙስና ትችት ሳቀርብ በቅርቡ የተጻፈው የ**Sarah Chayes, <u>Thieves of State: why corruption threatens global security</u>, 2015** መነበብ አለበት እላለሁ። የሃገር መፈራረስና የእርስ በእርስ ጦርነትን መንስኤዎች መሰረት በማድረግ ደራሲዋ የምትለው በግብጽ፤ በሶሪያ፤ በሊቢያ፤ በአፍጋኒስታን፤ በኢራክ፤ በፓኪስታን፤ በናይጀሪያና ሌሎች እርጋታና ሰላም የሌለበት፤ ሽብርተኞችና ተገንጣዮች ከፍተት ያገኙበት ወዘተ ሃገሮች ሆነዋል ትላለች። ለዚህ ዋናው ምክንያት በመንግሥትና ገዢ ፓርቲዎች ደረጃ የሚካሄደው <u>ኪራይ ሰብሳቢነት ሙስናና ዘረፋ</u> አደገኛ ደረጃ ላይ በመድረሱ ነው። ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ጉቦና ሙስና የተለመደ ቢሆንም፤ ክብደቱ፤ ጥልቀቱና ጉዳቱ ከሃገር ወደ ሃገር ይለያያል። የማይካደው በማስረጃ የተደገፈ ሃቅ የሚያሳየው ክስተት በቅርቡ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይፋ ከሆነው ጥናትና ግኝቶች ጋር ተመሳሳይ ነው። ይኼውም፤ በመንግሥትና ፓርቲ የበላዮች ደረጃ የሚደረግ ሙስና ሃገር ያጠፋል፤ የእርስ በእርስ ግጭት ያመጣል፤ የገቢና የኃብት ስርጭት ልዩነት ይፈጥራል፤ ለስደት መጋቢ ይሆናል፤ ለአመፀኞች መግቢያ ይሆናል፤ ለእድገት ጸር ነው ወዘተ። ከዚህ ጋር የተያያዙ ብዙ ምሳሌዎች አሉ። ሁለቱን እጠቅሳለሁ። **Alberto Alesina, Stelios Michalopoulos and Elias Papaioannous, <u>Ethnic Inequality,</u> Journal of Political Economy** በተባለው ጥናታቸው የአስተዳደር በደል፤ ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ጉቦ፤ ሙስናና ጎሳዊ አድልዎ ለፍትሃዊ እድገት ፀር መሆናቸውን አሳይተዋል። <u>መቶ ሰባ ሶስት (**173**) ሃገሮችን ወስደው **2,173** ጎሳዎችንና **7,581**</u> ልዩ ልዩ ቋንቅቋ ተናጋሪዎችን መሰረት አድርገው "ጨለማ ሲሆን የትኞቹ ዜጎች ሙብራት እንዳላቸው" ተመራምረዋል። "ብዙና ደማቅ ሙብራት የሚበራባቸው ጎሳዎችና የቋንቋ ክፍሎች የተሻለ ኑሮ እንደሚኖሩ፤ ጨለማ የሆኑት ግን ድሃ እንደሆኑ" ደምድመዋል። በአንድ ሃገር ውስጥ የሚኖሩ ዜጎች የተለያየ የእድገት እድል ለምን ተከስተባቸው የሚለውን ጥያቄ ሲመልሱ እንዲህ ብለዋል። **"The association between <u>inequality and development</u>" depends on the "proactive intervention by the government in power. If an <u>ethnic group</u> weilds political power, it tends to favor its own ethnic group at the exclusion of other ethnic groups."** ጎሳዊ "የፖለቲካ ባለሞያዎቹ ጎሳዊና ቡድናዊ የፖለቲካ ስልጣን ስለየዙ የተዛባ ገቢ፤ ኃብትና ኑሮ ይፈጠራል፤ የተዛባ መሰረተ ልማት ያስተጋባል" ከሚል ድምዳሜ ላይ ደርሰዋል።

**"Sub-Saharan Africa and East and South Asia are the most ethnically unequal regions," adds Chayes, "thanks to no small part, to <u>minority ethnic groups</u> who prospered under an exclusionary governance system that selects "winners and losers."** ጠባብ ጎሰኞች አድልዎ ማድረጋቸውና የተዛባ እድገት፤ ገቢና የኃብት ስርጭት መፍጠራቸው ምን የሕብረተሰብ ችግር ያመጣል? ከገቢ፤ ሃብትና ኑሮ መዛባት ሌላ ጥናቶቹ የሚያሳዩት፤ የምርት ኃይሎች በተፈለገው ደረጃ እንደማይጨምሩ፤ የተገለሉት ዜጎች፤ በተለይ ወጣቱ ትውልድ ወደ አመጻኛነት እንደሚሸጋገር፤ ሽብርተኞች አመች ሁኔታ እንደሚኖራቸው፤ ቀስ በቀስ እርጋታ እንደሚደፈርስና

የእርስ በእርስ ግጭት እንደሚነሳ ነው። ችግሩ የሃገር ውስጥ ከሆነ የዓለም ትሥስር (**Globalization such as FDI**) እና የውጭ እርዳታ ምን ተጽእኖ ይኖረዋል? መልሱ ብዙ የሚል ነው።

እርዳታን አግባብና ሃላፊነት ባለው መንገድ የተጠቀሙ ሃገሮች ከድህነት ነጻ የመውጣትና ራሳቸውን የመቻል እድላቸው ከፍ ያለ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ። ሆኖም እርዳታው በፍጥነት ውጤት ማሳየት አለበት ይላሉ። ስለዚህ፤ እርዳታ ዋጋ ቢስ ነው ለማለት አይቻልም። በሌላ በኩል የመንግሥት ስርዓቱ ብኪራይ ሰብሳቢነት፤ በአድልዎ፤ በጎሰኛነትና በአምባገነንነት የተበከለ ከሆነ የሚሰጠው እርዳታ ይባክናል፤ ይሰረቃል፤ ከሃገር ይሸሻል ወዘተ። የልማት ልሂቃን የሚሉት፤ እኔም የምጋራው ለጋሶች ስንት ዶላር ሰጡ የሚለው ሳይሆን፤ እያንዳንዱ ዶላር ከምን ጥቅም ላይ ዋለ፤ የስንቶቹን ዜጎች ህይወት አሻሻለ፤ ሃገሪቱ ከጥገኝነት ነጻ እንድትሆን ረዳ ወይንስ አልረዳም? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው። **"For decades, rich countries have sought to foster global development with aid….but there is little to show for their spending, now over $135 billion a year and rising…Success depends on actable, competent and responsible government that is bribery and corruption free<u>. It is political governance that determines outcomes</u>."** ኢኮኖሚስት የተባለው መጽሄት በ **May 23, 2015** ባወጣው ዘገባ እርዳታ ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገበት እንደሚባከን አሳይቷል። ትንተናውንና ድምዳሜውን ሙሉ በሙሉ እጋራለሁ። ዛሬ በኢትዮጵያ የሚካሄደው ድርጅታዊ ኪራይ ሰብሳቢነትና ምዝበራ ለሃገር አድሚ፤ አድካሚና አጥፊ እየሆነ ሂዷል። የተዛባ ገቢ፤ ኑሮና ኃብት እንዲፈጠር አድርጓል። ለጋስ ድርጅቶችና መንግሥታት ዘረፋውን እያዩ እንዳላዩ ማለፋቸው ያስገርመንና ያስቆጣን ይሆናል። ለጋስች ከእርዳታው ጥቅም ካላገኙበት እርዳታ አይሰጡም።

ኪራይ ሰብሳቢ የሆነ ቡድን ሁሉንም ነገር ለሽያጭ ያቀርባል፤ ሊሸጠው የማይችል አየሩን ብቻ ነው። ይኼን ሻየስ በግልፅ አቅርባዋለች። **"When <u>every government function is up for sale</u>---Ethiopia is a lead example of this in the areas such as land grab and sales---violations of international as well as domestic law become the norm."** ስርዓቱ ከሕግ ውጭ ስለሚሰራ፤ የሃገር ውስጥና የውጭ ተጠቃሚዎቹን ስርጭት ማስፋፋት ግዴታው ነው። **"The network of beneficiaries is diversified and globalized making it normal and part of doing business under global capitalism…External finance catalyzes systemic corruption because the potential yield of the practice to the donor is substantial."** አንዳንድ ታዛቢዎች የኢትዮጵያ መንግሥት ያደረገው ጥናት የአበዳሪዎችንና የለጋሶችን እምነት ለመግዛት ነው የሚሉት ለዚህ ነው። መንግሥት ችግሩን ተገንዝቦ ጥገናዊ ለውጥ ካደረገ እምነት ይኖራል፤ ካላደረገ ብድር ለማግኘት ከማይቻልበት ደረጃ ላይ የመድረስ እድል ይኖራል የሚል። ለዚህ መልስ የለኝም። ችግሩ ከአበዳሪዎች በላይ እንደሆነ አምናለሁ።

ከላይ ያቀርብኩትን የጥቅም ትሥስር በይፋ የማየው በአሜሪካና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ያለውን መደጋገፍ በቅጡ ሳጤነው ነው። የአሜሪካ መንግሥት የኢትዮጵያ መንግሥት በተከታታይ ሰብአዊ መብቶችን መግፈፉን ተቀብሎ ክብደትና ተቀዳሚነት የሰጠው በፀረ-ሽብርተኛው ዘመቻ የኢትዮጵያ መንግሥት ታዛገር፤ "ፈረስ ጫን ሲሉት ወደ የት" የሚል አገልጋይ ወይንም የአካባቢው ፖሊስ ሆኖ ለሚሰጠው አገልግሎት ነው። በተመሳሳይ፤ የውጭ ኢንቬስተሮች ትርፍ እስካገኙ ድረስ ሰብአዊ መብቶች ቢገፈፉ፤ እልቂት ቢኖር፤ ኪራይ ሰብሳቢነት ሕብረተሰቡን ቢያደማ፤ ድህነት ጥልቀት ቢይዝና የኢትዮጵያ ሉዐላዊነት ቢበረዝ ደንታ የላቸውም። በውጭ እርዳታውም የሚታየው ክስተት ተመሳሳይ ነው። የገዢው ፓርቲ ደጋፊ መንግሥታትና እርዳታ ሰጭዎች በኢትዮጵያ ለሚካሄደው ስርዓት ወለድ ጎሳዊ አድልዎ፤ ኪራይ ሰብሳቢነት፤ ሙስናና ከሃገር በገፍ ለሚሸሽ ሃብት ተባባሪ ወይንም አጋልማሽ፤ የቻየስን መሰረተ ሃሳብ ለመጠቀም አጋልማሽ (**enablers**) ሆነዋል። **"Insofar as kleptocratic govermments are functioning criminally, then their facilitaors (Aid, FDI, Military and Security Assistance) are accessories. They bear some moral responsibility if not currently material responsibility---not just for the criminal behavior, but for the often dramatic and destabilizing and expansive reactions it sparks."**

አንዳንድ የውጭ ልሂቃንና ግለሰቦች ከዘረፋው ጥቅም ስለሚያገኙ በታዳጊ ሃገሮች ሙስና የተለመደ ነው፤ እድገቱ ጥልቀት እየያዘ ሲሄድ ሙስናው ይቀንሳል ይላሉ። እኔ የምከራከረው እስከዚያ ሃገር ትጠፋለች፤ እልቂት ሊከሰት ይችላል ነው። ድህነትና ረሃብ አሰቃቂ ይሆናሉ። ወገኖቻችን የበረሃና የውቅያኖሶች ሰለባ እየሆኑ እያየን ይኼን የሚዘገንን ኪራይ ሰብሳቢነትና ዘረፋ ለማቆም ዛሬ ድምጽ ካላሰማን ሃገራችን የማጣት እድላችን ከፍ ያለ ነው። ይኼን ለግል ጥቅም ብለው አፋኝ አገዛዝን፤ ጎሳዊ

አድልዎን፤ ሙስናንና ከሃገር የሚሸሽ ኃብትን እንደ ተለመደ ጉዳይ የሚቆጥሩ የሃገር ውስጥና የውጭ ልሂቃንን ጎጅነት ከማንም በበለጠ ደረጃ **William Easterly, <u>the Tyranny of Experts: Economists</u>, <u>Dictatorships and the Forgotten Rights of the Poor</u>, 2013** በተባለው መፅሃፉ አቅርቦታል። ኢስተርሊ የኢትዮጵያን ድህነት በጥልቀት ከሚያውቁ የእድገት ሊቃውንት መካከል አንዱ ነው። ለጋስ ሃገሮች፤ ድርጅቶችና አገልጋይ የሆኑት ልሂቃኖቻቸው በእድገት ስም ትኩረት የማይሰጡት ለአምባገነናዊ መንግሥታት መሆኑን በተደጋጋሚ በማይታበል ማስረጃ አቅርቧል። የሚለው ከዓለም ባንክ የተለየ ሃሳብ ነው። **"Another view of <u>bad government---</u>also known as oppressive institutions---is that wherever people lack rights, and when oppression pays off for the rulers, the rulers will oppress their subjects" even more than they have done in the past. "Unchecked power is abusive power."** የኢትዮጵያ መንግሥት ጭካኔ ለምን እየከፋ ሄደ የሚለውን ጥያቄ በከፊል ይመልሰዋል። የፖለቲካ ስልጣን ከፍተኛ ገቢና ኃብት ማካበቻ ሲሆን ይኼን ስልጣን ለሌላ ለማስተላለፍ አስቸጋሪ ነው። በሌሎች ሃገሮች የሚካሄድ መሆኑ ባያከራክርም በኢትዮጵይ ታሪክ ውስጥ ህወሓት/ኢህአዴግ ለስልጣን ብልግናና ለኪራይ ሰብሳቢነት ዋና ምሳሌ ሆኗል። በአፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት "ኪራይ ሰብሳቢ" የሚለው ቃል ሲነገር አላስታውስም፤ በደርግም ጊዜ አላስታውስም።

ምንም እንኳን ስለ ሰብአዊ መብቶች ለመናገር ባይችልም--ዓለም ባንክ አይፈቅድም--በኢትዮጵያ የአለም ባንክ ዲሬክተር የነበረው ኬን ኦሃሺ የገዢውን ፓርቲ የአምስት ዓመት እቅድ የፖሊሲና የመዋቅር ድክመቶች አስመልክቶ የሰጠው ትችት አግባብ አለው። በዓለም ባንክ ታሪክ ውስጥ መለስን የተከራከረ እሱ ብቻ ነው። በአጭሩ የተቻቸው፤

አንድ፤ መንግሥት ያላተኮረው በኢትዮጵያ ተመጣጣኝ ጥሪቶች፤ አቅምና ተወዳዳሪነት አይደለም የሚል ...**"The Government is not focusing on Ethiopia's comparative advantage."**

ሁለት፤ መንግሥት በአስተዳደር በኩል ያለውን ግዙፍ የሆነ ወጭ ለመቀነስ አልቻለም የሚል...እንደ አሸን የበዛውን ስብሰባም የጨመረ ትችት ነው። **"The government is unable to reduce the transaction costs of doing business for the private sector."** በተደጋጋሚ በመጽሃፎቹና ሃተታዎቹ እንዳሳየሁት፤ ህወሓት/ኢህአዴግ የፈጠራቸው ተቋሞችና በብቸኝነት የሚቆጣጠረው መንግሥት የኢኮኖሚ የበላይነቱን ስለያዘ ተወዳዳሪ ሊሆን የሚችለውን የግል ክፍል በልዩ ልዩ ጫናዎች እንዳይፋፋ አድርጓል። አመራሩ ችግሮችን በመወያየት፤ በመተሳሰብና በመናበብ ለመፍታት ፈቃደኛ አይደለም። መለስን ያስቆጣው አባባል የሚከተለው ነው። **"The key to the GTP's success is the shift in the driver of growth from the public sector <u>to the private sector</u>."**

ሶስት፤ ኦሃሺ ያሳሠበው መንግሥት ከባንኮች በገፍ የሚበደረውና በብሄራዊ ባንኩ አማካይነት እያተመ የሚያሰራጨው ብር የተራውን ሕዝብ የመግዛት አቅም አድክሟል፤ ለዋጋ ግሽበት አስተዋፆ አድርጓል የሚል ነበር። ብዙ ዋጋ ቢስ ብር የተወሰነ አቅርቦት ለመግዛት ይሞክራል ማለት ነው። ኪራይ ሰብሳቢና ሙሰኛ በሆኑ ሃገሮች ሁሉ ገንዘብ በገፍ ይታተማል፤ ይሰራጫል፤ ዋጋ ቢስ እየሆነ ይሄዳል። ለመግዛት የሚችለው ኪሱ የሞላው ብቻ ነው። **"The government is taxing the banking system."** የገዢው ፓርቲ አመራር ባንኮችን እንደራሱ የግል ሂሳብ ቤት አድርጎ እንደምትታለብ ላም አልቧቸዋል፤ አሁንም እያለባቸው ነው። ይኼ በመሆኑ፤ የግል ክፍሉ እንደልቡ ብድር ለማግኘት አልቻለም። በተጨማሪ፤ ተወዳዳሪነት በሌለበትና የጥቁር ገበያው በሰፋባት ኢትዮጵያ የእድገትና የገበያ እንቅስቃሴ ጉቦ፤ የአስተዳደር ጎሳዊ አድልዎና ሙስና በመንግሥትና ፓርቲ ባለሥልጣናት ደረጃ ተቋማዊ ሆኗል። ፓርቲውና መንግሥት ያልገቡበት ተቋም ስለሌለ የባለሥልጣናት ሌቦች የሌሉበት ክፍል የለም። ፊት ለፊት የሚጠቀሙት ደላላዎችን መሆኑ ይፋ ሆኗል። ለኪራይ ሰብሳቢነትና ለሙስና አመች ሁኔታን ከሚፈጥሩት እንቅስቃሴዎች መካከል የመንግሥት የግንባታ ስራዎች ይገኙበታል--መንገድ፤ ድልድይ፤ ግድብ፤ ትምህርት ቤት፤ የመሰብሰቢያ አዳራሾች፤ የውሃ፤ የቴሌፎንና የመብራት አገልግሎት ወዘተ ስራ ዋናወቹ ናቸው። **"Huge financing for public investments (<u>often sole sourcing</u>) investment have led to measures that are destabilizing the macro framework, imposing a heavy inflation tax, raising costs for public investment projects, and <u>crowding out the private sector</u>."** ይኼ በተደጋጋሚ ሲካሄድ ድህነት በመቀነስ ፋንታ ጥልቀት ይይዛል፤ መዋቅራዊ ሆኖ ይቆያል፤ ለመፍታት ያስቸግራል። የኢኮኖሚውን መርህ አድሏዊ የመንግሥት ካፒታሊዝም **(<u>Crony State</u> <u>Capitalism</u>)** የሚያስብልና ለአገዛዛዝ ወለድ ኪራይ ሰብሳቢነትና ሙሰኛነት አመች ትርጉም

ይሰጣል። የዚህ አይነቱ የኢኮኖሚ አመራር በግልፅነት፤ በውድድር፤ በሕግ የበላይነት አያምንም፤ ለጥቂቶች አገልጋይ መሆኑ ነው። የውጭ እርዳታ አጠቃቀሙ የዚህ ሰለባ ሆኗል ለማለት እደፍራለሁ።

Terrence Lyons, Ethiopia: assessing risks and stability, June 2011 ስመለከት የችግሩ ጥልቀት በሺንገላ የማይፈታ መሆኑን እገነዘባለሁ። በኢትዮጵያ ጥልቀት እውቀት ያለው ላየንስ የፈተሸው በማህበራዊ ኑሮ፤ በኢኮኖሚውና በፖለቲካው ያለውን ግንኙነት ነው። የጠየቀው ጥያቄ እነዚህ "ግንኙነቶች ላለመረጋጋትና ለለውጥ ቀስቃሾች ናቸው ወይንስ አይደሉም፤ ከሆኑ ለምንና እንዴት" የሚል ነው። "የኢህአዴግ የጎሳ ስብስብ ፓርቲዎች የሚመሩት መንግሥት አምባገነን፤ ከፋፋይ፤ ግጭት ፈጣሪ" መሆኑን ይናገራል። ገዢው ፓርቲ "ጠባብና ጎሰኛ ነው፤ 98 በመቶ የሚሆነው የመከላከያ፤ የፌደራል ፖሊስና የስለላ መረብ የሚመራው በትግራይ ተወላጆች ነው። ህወሓት/ኢህአዴግ ህይወቱን ያራዘመው የሌሎችን ታማኝነት በመግዛት፤ ተቃዋሚውን በመከፋፈል፤ ሕብረተሰቡን በማስፈራራትና ለአባላትና ደጋፊዎች ድጎማ በመስጠት ነው" ይላል። "The country could erupt in unpredictable and dramatic ways" as it did under the previous two regimes. ይኼን ሲል በባዶው አይደለም። አምባገነን መንግሥታት ጠብ ጫሪ ስለሆኑ መሰረታዊ እርጋታ የላቸውም። የገዢውን ፓርቲ በኃይል የተመሰረተና ሃይል የሚጠበቅበትን ቆይታ አይቶ ዘላቂነት አለው ማለት "ስህተት ነው" ይላል። "An intolerance of dissent is deeply rooted in Ethiopia's political history, which has the effect of delegitimizing the types of peaceful opposition in more inclusive, democratic countries." ገዢው ፓርቲ አገዛዙን ያጠነከረው የመንግሥቱን ተቋሞች በሙሉ የራሱ መሳሪያ በማድረግ ነው። "In addition to its complete dominance of local and national government institutions, a number of large businesses are linked to the ruling party, either directly or through family members" and endowments. ይህ የገዢ ፓርቲ፤ የመንሥትና የሚቆጣጠራቸው የጥቅም ግንኙነቶች የኪራይ ሰብሳቢነት ባህሉን አስፋፍቶታል። ተራው ኢትዮጵያዊ በአገሩ ተስፋ የሚቆርጠው በዚህ ምክንያት ነው።

ላየንስ ህወሓት የፈጠረውንና አገር አቀፍ ሚና የሰጠውን የመንግሥት አይደለም የሚባለውን፤ ቢያንስ ሃያ የተለያዩ ድርጅቶችን የሚቆጣጠረውን Relief Society of Tigray (RST) እና የተቆራኘውን EFFORT ሚና ከፌደራሉ መንግሥትና ከውጭ ለጋሶች የሚገኘውን ድጋፍና ድጎማ ለድርጅቱ አባላት አገልግሎት ማዋሉን አሳይቷል። ከላይ እንዳቀረብኩት፤ የፖለቲካ ስልጣን መያዝና ማስከበር ለአዲስ ሃብታምነት ዋና መሳሪያ መሆኑ አያከራክርም። አንዱ የህወሓት አመራርና የተጠቃሚዎች ፍርሃት የመንግሥት ለውጥ ቢመጣ ያካበትነውን ኃብት የማጣት ሁኔታ ይፈጠራል የሚል እንደሆነ እገምታለሁ። እኔ የምከራከረው አማራጮች ስናቀርብ ይኼን ሃቅ መሳት የለብንም የሚል ነው። ላየንስ የሰነዘራቸው ሁለት ተጨማሪ ሃሳቦች አሉ። ኢኮኖሚውን በሚመለከት "Beyond the question of rates of growth in the past, the EPRDF will face increased political tensions if the economy stagnates or if high levels of inflation constrict the regime's resources base…" ካልጨመራቸው አበይት ጉዳዮች አንዱ፤ መንግሥት ተገቢውን ታክስ ለመሰብሰብ አለመቻሉ ነው። ሌላው የአሁኑ ሁኔታ ሕብረተሰቡን እንዳስቆጣውና የወደፊቱ ሁኔታ አስተማማኝ አለመሆኑን ነው። የኢኮኖሚው እድገት ዝቅ ማለት ብቻ አይደለም ችግሩን የሚያባብሰው። ልዩ ልዩና ተደራራቢ የመንግሥት ጫናዎች--ግልጽነትና ሃላፊነት አለመኖሩ፤ የሰብአዊ መብቶች መረገጣቸው፤ የተቃዋሚ ፓርቲዎች መገለላቸውና የሰላማዊው የትግል አማራጭ መዘጋቱ፤ የስራ እድል መጥፋቱና ወጣቱ ትውልድ መባከኑ፤ የኑሮው ውድነት መባባሱ፤ የኃይማኖት ነጻነት መገፈፉ-ተደማምረው ጨለማ የሆነ ሁኔታ ፈጥረዋል። ከላይ እንዳሳሰብኩት፤ ገዢው ፓርቲ ቢያውቅበት ችግሮቹን ከተቃዋሚው ክፍልና ከማህበረሰብ ድርጅቶች ጋር ተደራድሮ ለመፍታት ፈቃደኛ የመሆን እድል አለው። በፍርሃት ስለተወጠረ ተቃዋሚዎችን በገፍ ማሰሩ፤ ለመሪነት ይበቃሉ የሚባሉትን ማሳደዱና መግደሉ፤ የታሰሩትን አለመፍታቱ ወዘተ ሁኔታውን አባብሶታል።

ይኼን ክፍል ለማጠቃለል ባለሞያዎቹ ያልነኩት የፖለቲካው አገዛዝ ጉዳይና ከገዢው ፓርቲና ከመንግሥት ውጭ ተሳትፎ አለመኖሩ ጥናቱንና ግኝቶቹን ደካማና ጠባብ አድርጓቸዋል። የምጨምረው አስኳል ጉዳይ የመልካም አስተዳደር ችግሩን ያባባሰው የተቃዋሚው ክፍል መበታተንና መከፋፈል መሆኑን ነው። የፈለገውን መስዋእት ከፍሎ የሚታገልና ተባብሮ ለመደራደር የሚችል የተቃዋሚ ኃይል ቢኖር ይኼን እድል ተጠቅሞ የተሻሉ አማራጮችን ለማቅረብ ይቻል ነበር። አሁንም እድሉ እንዳያመልጥ ከተፈለገ አብሮና ተባብሮ ለመስራት ጥሪዎች መደረግ አለባቸው። ላየንስ እንዳለው "The opposition is divided, weak, often poorly led, and distracted by agendas of the increasingly

**disconnected diaspora.”** የምናውቀውም ቢሆን ይኼን ችግር መካድ የለብንም። “የእኔ ድርጅት፤ የእኔ ሃሳብ፤ የእኔ ታሪክ፤ የእኔ ፕሮግራም፤ የእኔ ህይወት ወዘተ” እያልን ገንቢ የሆነ አስተዋፆ ለማድረግ አንችልም። እያንዳንዳችን ራሳችን መርምረን፤ አውቀንና ለውጠን ለአገራችንና ለመላው ሕዝቧ በጋራ ለመቆም መቻል ታሪካዊ ግዴታችን ሆኗል።

ይኼ እንዳለ ሆኖ የኢትዮጵያ ኋላ ቀርነት፤ ለሕሊና የሚቀፍ ረሃብና ጥገኛነት፤ የአብዛኛው ሕዝብ የገቢ ድህነት ሊቀረፉ ይችላሉ የሚል እምነት አለኝ። ይኼ ስኬታማ የሚሆነው ሁሉም ኢትዮጵያዊያን መብታቸውና ክብራቸው ተጠብቆ በአገራቸው አመራር፤ ፖሊሲና እድገቶች ሙሉ ተሳታፊ ሲሆኑ ብቻ ነው። ገዢው ፓርት በተናጠል የኢትዮጵያን ግዙፍ የአገዛዝና የእድገት ችግሮች ሊፈታ አይችልም። ከፍተኛ ኪራይ ሰብሳቢዎችና ያመረቷቸው ደላላዎች የሕብረተሰቡን ችግሮች ይፈታሉ የሚል እምነት የለኝም። የእነሱ ዋና ዓላማ ትርፍ አግኝቶ መሸሸ ነው። እንደገና ከፍተቶችና ግድፈቶች ቢኖሩም፤ ባለሞያዎቹ ያቀረቡት ጥናት፤ ምርምርና ግኝቶች የሚናቁ አይደሉም። የሌሎቻችን ሃላፊነት የችግሩን መዋቅራዊና ስርዓታዊ (Structural and Systemic) ጥልቀትና ክብደት በማጤን ገንቢ የሆኑ በጥናትና ምርምር የተደገፉ አማራጮች ለውይይትና ለድርድር እንዲቀርቡ መግፋት ነው።

11/2015